# በኢትዮጵያ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የጋብቻ ፡ አቋም ።

ከዊልያም ፡ ቡሐጂየር ፡
የኢትዮጵያ ፡ ከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡
ፕሬዚዳንት ።

በውእነቱ ፡ በክርስቲያኗ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ እንደነበረው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ጋብቻ ፡ ያንድ ፡ ላንድ ፡ ኅብረት ፡ ነው ፡ ማንኛውንም ፡ ሌሎች ፡ ሰዎችን ፡ ሳይጨምር ፡ አንዱ ፡ ወንድና ፡ አንዲ ፡ ሴት ፡ በነዛኛቸው ፡ የሚጋቡበት ፡ የፈቃድ ፡ ሱታፌ ፡ ነው ። ሕጉ ፡ ሦስት ፡ የጋብቻ ፡ ዐይነቶችን ፡ —(1) ብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፡ (2) የሃይማኖት ፡ ጋብቻን ፡ (3) የልማድ ፡ ጋብቻን ፡ ያስተነትናል ። ጋብቻ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከሴህ ፡ ሥርዓቶች ፡ በማናቸውም ፡ አንዱ ፡ ዓይነት ፡ ሥርዓት ፡ ሊከናወን ፡ ይችላል ። ነገር ፡ ግን ፡ በባልዩውና ፡ በሚስቲቱ ፡ መካከል ፡ በሚመለከተው ፡ የግል ፡ ዝምድና ፡ (ግንኙነት ፡ ) ሆነ ፡ ወይም ፡ ሀብታቸውን ፡ በሚመለከተው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በሁለቱም ፡ በኩል ፡ ጋብቻው ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ በሦስቱም ፡ የጋብቻ ፡ መልኮች ፡ ያው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ውጤትን ፡ ነው ፡ በልማድ ፡ ጋብቻም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። ስለምን ፡ ቢሉ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ጋብቻው ፡ የተከናወነው ፡ የባልየውን ፡ ወይም ፡ የሚስቲቱን ፡ የወግና ፡ ልምድ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተከትሎም ፡ ቢሆን ፡ ቅሉ ፡ የጋብቻው ፡ ውጤቶች ፡ የሚጻኙት ፡ ጋብቻው ፡ በተከናወነበት ፡ የልማድ ፡ ሕግ ፡ ሳይሆን ፡ በሕጉ ፡ (ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ) ድንጋጌዎች ፡ እንዲሆን ፡ ሲባል ፡ ነው ፡ ይላል ።

ብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፡ ማለት ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዝግብት ፡ ሹም ፡ ፊት ፡ የሚፈጣጠሙት ፡ ጋብቻ ፡ ነው ። የሃይማኖት ፡ ጋብቻ ፡ ማለት ፡ በሁለቱም ፡ ወገኖች ፡ ወይም ፡ ከነሱ ፡ ባንዱ ፡ ሃይማኖት ፡ ያፈጸጸም ፡ ሥርዓቶች ፡ መሠረት ፡ የሚሾመው ፡ ጋብቻ ፡ ነው ። (እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሃይማኖት ፡ ቢሸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይም ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ ያፈቀደው ፡ የሌላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ እምነት ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። ) የልማድ ፡ ጋብቻ ፡ የሚባለው ፡ በነበሮቹ ፡ ነገድ ፡ ወይም ፡ ከዓበሮቹ ፡ ባንዱ ፡ ነገድ ፡ ወግና ፡ ሥርዓት ፡ ኑዋሪ ፡ የሆነውን ፡ ጥምረት ፡ ሲያቋቋሙ ፡ ነው ። ቀድሞ ፡ በደመወዝ ፡ ይባል ፡ የነበረው ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ የታወቀ ፡ አይደለም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ቆየት ፡ ብለን ፡ እንደምናየው ፡ ሁሉ ፡ በዚሁ ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻ ፡ ፈንታ ፡ ወዶገብ ፡ ኅብረት ፡ የተባለውን ፡ በተወሰነ ፡ አኳኋን ፡ በፍርድ ፡ የታወቀውን ፡ ባንድ ፡ ወንድና ፡ ባንድ ፡ ሴት ፡ መካከል ፡ ያለን ፡ ሀልው ፡ ሁኔታን ፡ ሕጉ ፡ ይተካል ።

## ፩፡ ለማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻዎች ፡ የሚያገለግሉ ፡ የውል ፡ ግዴታዎች ።

### ግዴታዎች ፤

ከላይ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ሦስት ፡ ዓይነት ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዓቶች ፡ በማናቸውም ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ማንኛውም ፡ ጋብቻ ፡ ከመከናወኑ ፡ በፊት ፡ ሊፈጸሙ ፡ የሚገባቸው ፡ አንዳንድ ፡ ግዴታዎች ፡ አሉ ። እሊህም ፡ እንደሚከተለው ፤ ዕድሜ ፤ የሥጋ ፡ ዝምድናና ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ጥንድ ፡ ጋብቻ ፡ እና ፡ ለማግባት ፡ ፈቃደኝነት ፡ ናቸው።

፩፡ ዕድሜ ፤–በዕድሜው ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ያልደፈነ ፡ ወንድና ፡ በዕድሜዋ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ያልሞላት ፡ ሴት ፡ ጋብቻን ፡ ሊያደርጉ ፡ አይችሉም። ከዚህ ፡ ግዴታ ፡ ዝቅ ፡ በማድረግ ፡ ሊታደግ ፡ የሚችል ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወይም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ ሲል ፡ የሾመው ፡ ሰው ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ እንደ ዚህ ፡ ያለው ፡ ታዳጊነት ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ በታች ፡ ለመቀነስ ፡ አይፈቀድም ፤ ይኸውም ፡ በታዳጊነቱ ፡ መሠረት ፡ ከሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ላላነሰ ፡ ወንድና ፡ ከሥራ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ላላነሰች ፡ ሴት ፡ ጋብቻ ፡ ሊሾም ፡ ይቻላል ፡ ማለት ፡ ነው ። (ቍጥር ፡ ፭፻፹፩ ።)

፪፡ የሥጋ ፡ ዝምድናና ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፤– እሊህ ፡ የጋብቻ ፡ አደናቃፊዎች ፡ ናቸው ፡ በሥጋ ፡ በተዛማመዱና ፡ በጋብቻ ፡ በተዛማመዱ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ጋብቻ ፡ ክል ክል ፡ ነው ። (ቍጥር ፡ ፭፻፹፪ ፡ እና ፡ ፭፻፹፫ ።) እንዲሁም ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ በይታወቅላቸውም ፡ ቅሉ ፡ ዕርግጠኛ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅነት ፡ መተሳሰሪያቸው ፡ በይፋ ፡ በታወቀላቸው ፡ የሥጋ ፡ ዘመዳሞች ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዘመዳሞች ፡ መሆን ፡ በሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ጋብቻ ፡ እንዳይሾም ፡ ቍጥር ፡ ፭፻፹፬ ፡ ይከለክላል ። የሥጋ ፡ ዝምድናና ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ውስጠ ፡ ምስጢሩ ፡ በቍጥር ፡ ፭፻፺ ፡ እና ፡ በተከታታዮቹ ፡ ቍጥሮች ፡ ላይ ፡ ተተርጉሟል ።

፫፡ ጥንድ ፡ ጋብቻ ፡ ፤–ለማጋባት ፡ ከአቀዱት ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ በቀደመ ፡ ጋብቻ ፡ የተቀየደ ፡ ከሆነ ፡ የቀድሞው ፡ ጋብቻ ፡ እስካለ ፡ ድረስ ፡ በነዚህ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ጋብቻ ፡ ሊሾም ፡ አይቻልም ።(ቍጥር ፡ ፭፻፹፭ ።)

፬፡ ፈቃደኛነት ፤—እንደ ፡ ሌላው ፡ ውል ፡ ሁሉ ፡ ጋብቻም ፡ ነባር ፡ ዋጋ ፡ እንዲኖረው ፡ መሰይ ፡ ወገኖቹ ፡ ተፈቃቅደው ፡ እንዲስማሙ ፡ ያስፈልጋል ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ፈቃደኛነትም ፡ ነጻ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል፤ይኸም ፡ በኃይል ፡ አስገዳጅነት ፡ ያላስተፋት ፡ ፈቃድ ፡ እና ፡ በማናቸውም ፡ የሕላዌ ፡ ዝንጋታ ፡ ያልተበከለ ፡ ፈቃድ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። የጋብቻ ፡ በዓል ፡ በሚከናወንበት ፡ ጊዜ ፡ ዓበሮቹ ፡ ራሳቸው ፡ መፈቃቀዳቸውን ፡ እንዲያስታውቁ ፡ ይገባል ። ፈቃደኝነታቸውን ፡ ለማስታወቅ ፡ መሰዮቹ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሊወክሉ ፡ አይችሉም ፤ ይኸም ፡ ጋብቻ ፡ በእንደራሴ ፡ አይፈቀድም ፡ ማለት ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ሲኖር ፡ ጠቅላይ ፡ አቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ከዚህ ፡ መታደጊያ ፡ የሚሆን ፡ ፈቃድ ፡ ሊሰጥ ፡ ይችላል ፡ (ቍጥር ፡ ፭፻፹፮ ።) ኢአክል ፡ ( ያለ ፡ አክል ፡ ) ሰው ፡ በሚያገባበት ፡ ጊዜ ፡ የራሱ ፡ የኢአክሉና ፡ ቤተ ፡ ዘመዱን ፡ የወከለው ፡ ሰው ፡ እንደራሴ ፡ ፈቃደኝነት ፡ ያስፈልጋል ። በፍርድ ፡ የተወሰነ ፡ ሰውን ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ የራሱ ፡ ፈቃደኝነት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለዚሁ ፡ ሲል ፡ በሚሰጠው ፡ ፈቃድ ፡ መደገፍ ፡ ይገባዋል ፡ (ቍጥር ፡ ፭፻፹፯ ፡ እና ፡ ፫፻፴፱ ።)

## በኃይል ፣ አስገዳጅነት ፣ ወይም ፣ በህላዌ ፣ ዝንጋታ ፣ የተገኘ ፣ ፈቃድ ፣ ብልሹ ፣ ነው ፧

በኃይል ፣ አስገዳጅነት ፣ የተገኘ ፣ ፈቃደኝነት ፣ ንጹሕ ፣ ( ጥሩ- ነጻ ፣ ) ፈቃድ ፣ ስላ ልሆነ ፣ እንዳችም ፣ ዓይነት ፣ ፈቃደኝነት ፣ አይደለም ። ፈቃደኝነትን ፣ የሚያበላሽ ፣ ማና ቸውም ፣ ዓይነት ፣ የኃይል ፣ ተግባር ፣ አይደለም ፤ በቁጥር ፣ ፲፯፻፮ ፣ ( ፪ ፣ ) መሠረት ፣ ፈቃደኝነት ፣ የሚጐድፈው ፣ ራሱን ፣ ወይም ፣ ራሷን ፣ ወይም ፣ ከወራጅ ፣ ዘመዶቹ ፣ ወይም ፣ ከአውራጅ ፣ ዘመዶቹ ፣ አንዱን ፣ ከባድ ፣ ከሆነ ፣ ጉዳትና ፣ ዛቻ ፣ ለማዳን ፣ ሲል፡ በመጨነቅና ፣ በመገደድ ፣ የተፋው ፣ ፈቃደኝነት ፣ ሲሆን ፣ ነው ። እንዲህ ፣ ያለው ፣ ስቃ ይም ፣ የማይዳሰስ ፣ ረቂቅ ፣ የመንፈስ ፣ ወይም ፣ የሚዳሰስ ፣ ግዙፍ ፣ (የሚጨበጥ- ሥጋዊ ፣ ) ሊሆን ፣ ይችላል ። ይህ ፣ ጉዳት ፣ በጊዜ ፣ ርዝማኔ ፣ ሊያልፉት ፣ ወይም ፣ በማ ዘግየት ፣ ሊገፉት ፣ የማይቻል ፣ ከባድ ፣ ባሕርይ ፣ ያለው ፣ መሆን ፣ ይገባዋል ። ፍዳው ፣ ያልከበደ ፣ ወይም ፣ የማያሰጋ ፣ ሲሆን ፤ ፈቃደኝነትን ፣ ያስገኘው ፣ ኃይል ፣ ፈቃድን ፣ አያበላሸውም ። አውራጅ ፣ ዘመዶችን ፣ ወይም ፣ ማንኛውን ፣ ሌላ ፣ ሰውን ፣ በማክበርና ፣ በማፈር ፣ የገቡበት ፣ የፈቃደኝነት ፣ ቃል ፣ የጐደፈ ፣ አይደለም ፤ ይኸም ፣ አውራጅ ፣ ዘመድን ፣ (ለምሳሌ ፣ አባትን ፤ ወንድ ፣ አያትን ፤ ሴት ፣ አያትን ፤) ወይም ፣ ማንኛው ንም ፣ አውራ ፣ ዘመድ ፣ ባይሆን ፣ እንኳን ፣ <u>ዘመድ ፣ አካል ፣ ተብሎ ፣ የሚቆጠር ፣</u> ሌላ፣ ሰውን ፣ በማክበር ፣ የገቡበት ፣ ፈቃድ ፣ የተጓደለ ፣ አይደለም ፣ ማለት ፣ ነው ፣ (ቁጥር ፣ ፲፯፻፮ ፣ (፫) ።)

<u>ከህላዌ ፣ ዝንጋታ ።</u> የተነሣ ፣ ፈቃደኝነት ፣ የሚበላሸው ፣ ከአበሮቹ ፣ አንዱ ፣ ሌላ ውን ፣ ( መሳዩን ፣ ) ነክ ፣ ስለሆኑ ፣ አንዳንድ ፣ ጉዳዮች ፣ ሳያውቅ ፣ መስሎት ፣ ተሳስቶ ፣ ቃል ፣ የገባበት ፣ ፈቃደኝነት ፣ ሲሆን ፣ ነው ። ቁጥር ፣ ፲፯፻፲፩ ፣ ህላዌ ፣ ዝንጋታ ፣ ተብለው ፣ ፈቃደኝነትን ፣ ለማበላሸት ፣ በቂ ፣ የሚሆኑ ፣ የተወሰኑ ፣ ምክንያቶች ፣ ዝርዝርን ፣ ይሰ ጣል ። እሊህም ፣ እንደሚከተሉት ፤ –

ህ/ የመሳዩን ፣ አካል ፣ መዘንጋት ፣ (መሳት ፤) ወይም ፣

ለ/ የአበሩን ፣ ሃይማኖት ፣ መዘንጋት ፤ ወይም ፣

ሐ/ የመሳዩን ፣ ጤንነት ፣ ወይም ፣ ሰብአዊ ፣ ባሕርይ ፣ ችሎታ ፣ መዘንጋት ፣ ናቸው ።

የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕጉ ፣ ዝንጋታውን ፣ <u>በሚያገቡት ፣ ሰው ፣ አካላዊ ፣ ባሕርይ ፣</u> በሚመለከተው ፣ ጉዳይ ፣ ላይ ፣ መሆኑን ፣ ይወስናል ፤ ማለት ፣ መሳሳቱ ፣ በአበሩ ፣ <u>ባሕ ርያዊ ፣ አካል ፣ አቋም ፣</u> እንደሆነ ፣ አጉልቶ ፣ ይገልጣል ። ሕጉ ፣ የተገለገለባቸው ፣ ቃሎች ፣ በሌላ ፣ ሕጐች ፣ ዘንድ ፣ ከተነሡት ፣ አሻሚ ፣ ብዙ ፣ ክርክሮች ፣ ይገላግላሉ ። ለምሳሌ ፣ በፈረንሳይ ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ (ቁጥር ፣ ፩፻፹ ፣ (፪) ፣) እና ፣ እንደ ፣ ኤውሮፓው ያን ፣ አቆጣጠር ፣ በ ፲፱፻፵፪ ፣ ዓ ፣ ም ፣ የኢጣሊያን ፣ አገር ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ (ቁጥር ፣ ፩፻፶ ፣) ይ ፣ የሠፈሩት ፣ ቃሎች ፣ ‹እውሬር ፣ ሱር ፣ ላ ፣ ፐርሰን › (በሰብአዊነቱ ፣ ላይ ፣ መሳሳት ፣ ) እና ፣ « ኤሮሬ ፣ ኒላ ፣ ፔርሰና ፣ » ( በሰብአዊነቱ ፣ ላይ ፣ መሳሳት ፣ ) ነበሩ ። አከራካሪው ፣ ጉዳይ ፣ ሰብአዊነት ፣ ሲል ፣ ስለ ፣ አበሩ ፣ አካላዊ ፣ ባሕርይ ፣ ሲያ ጣይቅ ፣ ብቻ ፣ ነውን ? ወይስ ፣ እንዲሁም ፣ ስለ ፣ አበሩ ፣ ተፈላጊ ፣ የመለያ ፣ ጠባዮችን ፣ ጭምር ፤ (ለምሳሌ ፣ የምትገባውን ፣ ሚስት ፣ ድንግላይነትን ፣ የመሰለ ፣ ወይም ፣ አበሩ ፣ በወንጀለኛ ፣ መቅጫ ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ ተወንጅሎ ፣ መቀጣቱን ፣) የሚለው ፣ ጉዳይ ፣ ነው ። በኢትዮጵያ ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕግ ፣ መሠረት ፣ ግን ፣ የስሕተቱ ፣ መጠን ፣ ያከበው ፣ በአበሩ ፣ <u>አካላዊ – ባሕርይ ፣</u> ላይ ፣ መሳሳትን ፣ ነው ። ለማስረጃ ፣ ያህል ፣ ከፖ

ቷዩ ፣ የተሰጠንን ፣ ትችት ፣ እናውሳ ፤ «ለምሳሌ ፣ ማሪን ፣ ለማግባት ፡ ቍርጥ ፡ አሳብ ፡ አደረግኩና ፡ ከማሪ ፡ ጋራ ፡ የተፈጣጠምኩ ፣ መስሎኝ ፣ ራሷን ፣ የማሪ ፡ አምሳያ ፡ አድርጋ ፣ ለማለፍ ፡ ለምትችለው ፣ ለገሮን ፡ የመሐላ ፡ ቃሌን ፣ ገባሁላት ፣ » የሚል ፡ ነው ። እንግዲህ ፣ በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕጉ ፣ መሠረት ፣ ስለ ፣ አበሩ ፣ በሕዝብ ፡ ማኅበር ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ የደረጃ ፣ አቋም ፣ (ሰሲያል ፡) ወይም ፡ ስለ ፡ አበሩ ፣ የገንዘብ ፡ ሀብት ፣ አቅም ፣ መሳሳት ፡ ወይም ፡ ስለ ፣ አበሩ ፡ ልዩ ፣ ግብሮች ፣ ( ጠባዮች ፡ ) ወይም ፡ ማናቸውም ፣ ሌላ ፡ ስሕተት ፡ ፈቃደኝነትን ፡ ሊያበላሽ ፣ አይችልም ።

<u>ስለመሳዩ ፡ ሃይማኖት ፡ መዘንጋት</u> ፡ ፈቃደኝነትን ፡ ሊያጓድል ፣ የሚችለው ፡ የመሳዩ ፡ ሃይማኖት ፣ ከተሳሳተው ፡ አበር ፣ ሃይማኖት ፡ የተለየ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፣ ብቻ ፡ ነው ፡ እነሆ ፣ በኢትዮጵያ ፣ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ሃይማኖት ፡ ያለ ፡ አንድ ፣ ወንድ ፡ ሊያገባት ፡ ያቀዳት ፣ ሴትዮ ፣ በእርግጡ ፡ በሱው ፣ ሃይማኖት ፡ ያለች ፡ ሳለ ፡ የግሪክ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፣ ሃይማኖት ፣ ልጅ ፣ ነች ፡ ብሎ ፡ ቢያስብ ፡ ፈቃድን ፡ ሊያጐድፍ ፡ የሚችል ፡ የሀላዌ ፡ ዝንጋታ ፣ የለም ፡ ማለት ፣ ነው ።

ስለጤንነት ፣ ሁኔታ ፣ መሳሳት ፡ የሚባለው ፣ አበሩ ፣ ጤነኛ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፣ ሲታመን ፣ ሳለ ፡ ደዌ ፣ ሥጋ ፣ የያዘው ፣ ሆኖ ፣ በሚገኘው ፣ ሰው ፣ ላይ ፡ የታከበ ፡ ነው ። ደግሞም ፣ የጋብቻን ፡ ጣዕም ፡ በምሉ ፣ ለማርከት ፡ የሚያገባው ፡ ሰው ፡ ስለሌላው ፣ አበር ፣ የሩካቤ ፡ ሥጋን ፣ ተግባር ፣ ለማከናወን ፡ ተፈላጊ ፣ ስለሆኑት ፡ አባሎች ፡ አቅም ፡ በተሳሳተ ፣ ጊዜ ፡ ፈቃደኛነቱ ፡ ለመጓደሉ ፡ በቂ ፡ ስሕተት ፡ አለማለት ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፣ መሳዩ ፡ ያባለ ፡ ዘር ፡ ደዌ ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፣ ከንደዚህ ፣ ያለው ፡ ደዌ ፡ የተነሳ ፡ አበሩ ፡ የሩካቤ ፡ ሥጋ፡ተግባርን፡ለመፈጸም ፣ የማይችል ፣ ካልሆነ ፣ በስተቀር ፣ ባባለዘር፡ ደዌ ፣ ይሠቃይ ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ የመሆኑ ፡ ሀልው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድን ፣ ለማበላሸት ፣ የሚበቃ ፡ የሀላዌ ፣ መሳሳት ፡ ሆኖ ፡ አይገመትም ።

በፍትሐ ፣ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፺፩ ፣ መሠረት ፡ ፈቃድኝነትን ፣ ለማጉደፍ ፡ በቂ ፣ የሀላዌ ፣ ስሕተቶች ፣ ሆነው ፡ የማይቆጠሩት ፡ ሌላውን ፣ ዐበር ፡ በሚመለከቱት ፡ ጉዳይ ፣ ላይ ፡ የተፈጸሙት ፣ ስሕተቶች ፡ ከባድ ፡ ያልሆነን ፡ የፍቺ ፡ ምክንያትን ፣ ሊያስከትሉ ፡ ይችላሉ ፤ ለምሳሌ ፣ አንዱ ፣ መሳይ ፡ ስለሌላው ፡ አበር ፣ በመልክም ፣ ጤንነት ፡ መኖር ፣ እምነቱ ፣ ማስረጃ ፡ እያለው ፣ ባባለ ፡ ዘር ፡ ደዌ ፣ ተበክሎ ፣ በሚገኝበት ፣ ጊዜ ፡ ነው ። እንደዚሁም ፣ ያንዳንድን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክፍል ፣ ሀገርን ፡ ወግና ፡ ሥርዓት ፣ ተከትለን ፣ ባልየው ፣ ሚስቲቱን ፣ ከነሕጓ ፣ ነች ፡ ብሎ ፣ አምኖ ፣ ሳለ ፡ የጋብቻው ፡ ዕለት ፣ ይኸው ፣ ሕጓ ፣ በይገኝ ፣ ለፍቺ ፡ መነሾ ፡ በቂ ፣ ምክንያትን ፣ ያቀርባል ፣ ብሎ ፡ ለማመን፣ ይቻላል ፣ እንጂ ፤ ጋብቻው ፡ የፈረሰበት ፡ (ዋጋ ፣ አልባ ፣ የሆነበት ፡ )ምክንያት ፡ ከሀላዌ፣ ስሕተቶች ፡ የተነሣ ፡ ፈቃደኝነቱ ፣ በመጓደሉ ፡ ነው ፣ አያሰኝም ።

## <u>ጋብቻው ፣ እንዳይፈጸም ፣ መቃወሚያ ፡ ማቅረብ ።</u>

የቍጥር ፡ ፫፻፺፫ ፣ ድንጋጌዎችንና ፣ ማናቸውም ፣ ዓይነት ፣ የጋብቻ ፣ ሥነ ፡ በዓል ፣ ከመከናወኑ ፣ በፊት ፡ ስለሚፈጽሙት ፣ ግዴታዎች ፣ በመመልከት ፣ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፣ ጋብቻን ፣ ለማገድ ፡ መቃወማቸውን ፣ ሕጉ ፣ ይቀበላል ። በቍጥር ፣ ፫፻፺፪ ፡ መሠረት ፣ እንደዚህ ፣ የመሰለውን ፣ ማገጃ ፣ ምክንያት ፣ ሊያቀርቡ ፣ የሚችሉት ፡ ሰዎች ፡ በዚሁ ፣ ቍጥር ፣ ውስጥ ፣ የተጠቀሱት ፣ እንጂ ፣ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፤ እነርሱም ፦

ሀ/ ከሚጣመሩት ፡ ያንዱ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ እንደራሴ ፡ (ይኸውም ፡ በቁጥር ፡ ፭፻፺፪ ፡ የተጠራውን ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የኢ.አስ.ሉ ፡ ጠባቂ ፡ ሞግዚትን ፡ ማለት ፡ ነው ፡) ለጋብቻው ፡ ከሚፈለገው ፡ ዕድሜ ፡ ደረጃ ፡ ባለመድረሱ ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ የሥጋ ፡ ወይም ፡ የጋቢ ፡ ዝምድና ፡ በመኖሩ ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ እንደራሴ ፡ ጋብቻውን ፡ ካለመፍቀዱ ፡ የተነሣ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ መቃወሚያ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ። አበሩ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ያገባ ፡ ሲሆን ፡ ማገጃ ፡ ምክንያትን ፡ ሊያቀርብ ፡ የሚችለው ፡ አቃቤ ፡ ሕግ ፡ ነው ። (ቁጥር ፡ ፭፻፺፩ ፡ (፪) ፡

ለ/ ለምሳሌ ፡ ያሀል ፡ ከሚጣመሩት ፡ ሰዎች ፡ መከከል ፡ አንዱ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በተደረገ ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ የተቀየደ ፡ ሆኖ ፡ ሲገኝ ፡ አቃቤ ፡ ሕግ ፡ ማገጃ ፡ መቃወሚያን ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።

ማገጃ ፡ ለማቅረብ ፡ ልዩ ፡ መልክና ፡ ሥርዓት ፡ እንዲደረግለት ፡ ሕጉ ፡ አልወሰነም ፡ የጋብቻው ፡ በዓል ፡ እስከሚከናወንበት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ማገጃ ፡ ምክንያቱ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ፡ (ቁጥር ፡ ፭፻፺፩ ፡) ። ከአበሮቹ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ መቃወሚያው ፡ እንዲቀር ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ፤ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ጥያቄ ፡ ሳይፈቀድለት ፡ ቢቀር ፡ ይግባኙ ፡ ከፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፊት ፡ ይዘረጋል ፡ ማለት ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በጋብቻው ፡ መቃወሚያ ፡ የቀረበበት ፡ ሰው ፡ ዕድሜ ፡ ከሃያ ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ የሆነ ፡ ሲሆንና ፡ ማገጃው ፡ የቀረበውም ፡ ወደፊት ፡ ከሚአብሩት ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ሁለተኛው ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ የመነጨ ፡ ሲሆን ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለው ፡ መቃወሚያ ፡ የይግባኝ ፡ አቤቱታ ፡ ሊኖረው ፡ አይችልም ። ይግባኙን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሰምቶ ፡ ማገጃው ፡ እንዲሻር ፡ ከበየነ ፡ በኋላ ፡ በእንደዚህ ፡ ያሉት ፡ አበሮች ፡ መከከል ፡ የጋብቻው ፡ በዓል ፡ እንዳይፈጸም ፡ እንደገና ፡ ማገጃ ፡ ሰበብ ፡ ለማቅረብ ፡ የተፈቀደ ፡ አይደለም ፡ (ቁጥር ፡ ፭፻፺፫ ።)

በቁጥር ፡ ፭፻፹፫ ፡ በተመለከቱት ፡ ማናቸውም ፡ ምክንያቶች ፡ የተነሣ ፡ የጋብቻ ፡ ዘመኑዋ ፡ ከፍጻሜ ፡ የደረሰበት ፡ ሴት ፡ (ይኸውም ፡ በባሏ ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ በፍቺ ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ግዴታዎች ፡ አንዱ ፡ በመጣሱ ፡ ምክንያት ፡ ጋብቻው ፡ የፈረሰበት ፡) የመጀመሪያው ፡ ጋብቻ ፡ ከተደመደመበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ቀኖች ፡ እስኪያልፉ ፡ ድረስ ፡ አዲስ ፡ ጋብቻ ፡ ለመዋዋል ፡ አትችልም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ፩፻፹ ፡ ቀኖቹ ፡ ከማለቃቸው ፡ በፊት ፡ ባለው ፡ በማናቸው ፡ ጊዜ ፡ ልጅ ፡ የወለደች ፡ እንደሆነ ፡ ይህ ፡ የንደገና ፡ ማግባት ፡ ክልከላ ፡ አይጸናባትም ። በወዶገብነት ፡ ኅብረት ፡ ካንድ ፡ ወንድ ፡ ጋር ፡ በኖረች ፡ ሴትም ፡ ላይ ፡ ይኸው ፡ ክልከላ ፡ ይረጋበታል ፡ (ቁጥር ፡ ፭፻፺፪) ። በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተመለከተው ፡ የመከልከል ፡ ተግባር ፡ አባትነትን ፡ በሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ከማናቸውም ፡ መዘነቅ ፡ ለመራቅ ፡ ሲባል ፡ ነው ፤ በፊተኛው ፡ ጋብቻ ፡ የተጸነሰ ፡ ሕፃን ፡ በማሕጸን ፡ መኖሩን ፡ ለመረዳት ፡ የ፩፻፹ ፡ ቀን ፡ ዕድሜ ፡ በቂ ፡ ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያገባች ፡ ሴትን ፡ የመበለትነት ፡ ጊዜዋን ፡ ከመጠበቅ ፡ ሊታደጋት ፡ ይችላል ። እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ታዳጊነት ፡ ለመስጠት ፡ የሚቻለው ፡ ለምሳሌ ፡ ሴትየዋ ፡ ልጆችን ፡ ለመውለድ ፡ አለመቻሏን ፡ ለማረጋገጥ ፡ በሚቻልበት ፡ አባትነትን ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ማናቸውም ፡ አጠራጣሪ ፡ ጉዳዮች ፡ ምንም ፡ ሥጋት ፡ በሌለ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

## ፪ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ ብጋቾዎች ፡ በዓል ፡ አከባበር ፡ ሥርዓቶች ።

ብሔራዊ፡ጋብቻ ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ከወላጆቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ከአውራጅ ፡ ዘመዶቹ ፡ አንዱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ጋብቻው ፡ ከሚከበርበት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ለስድስት ፡ ወር ፡ መኖሪያውን ፡ በቋቋመበት ፡ ሰፍራ ፡ ላይ ፡ በቀበሌው ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹም ፡ ፊት ፡ የሚፈጣጠሙት ፡ ጋብቻ ፡ ነው ፡ (ቊጥር ፡ ፭፻፺፯) ። ጋብቻው ፡ የሚደረግበት ፡ ዕለት ፡ በሚአብሩትና ፡ በሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ መካከል ፡ በስምምነት ፡ ይቆረጣል ፡ (ቊጥር ፡ ፮፻፮) ። የወደፊት ፡ አበሮቹና ፡ አራት ፡ (ማለት ፡ ለያንዳንዱ ፡ አበር ፡ ሁለት) ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ ጋብቻው ፡ በይፋ ፡ ይነገራል ፤ እነዚሁ ፡ ምስክሮችም ፡ ለወደፊቱ ፡ አበሮች ፡ ሊዛመዱ ፡ ወይም ፡ ላይዛመዱ ፡ ይችላሉ ፡ (ቊጥር ፡ ፮፻፫) ። የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ ጋብቻውን ፡ ከመሾሙ ፡ በፊት ፡ የወደፊት ፡ አበሮቹና ፡ ምስክሮቻቸው ፡ በሚያውቁት ፡ መጠን ፡ ጋብቻው ፡ እንዳይፈጸም ፡ የሚያስከለክል ፡ አንዳችም ፡ እንቅፋት ፡ (ለምሳሌ ፡ የሥጋ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ ) አለመኖሩን ፡ ገልጠው ፡ የመሐላ ፡ ቃላቸውን ፡ ይሰጣሉ ። መሐላ ፡ ከገቡም ፡ በኋላ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ ከሁለቱም ፡ አበሮች ፡ አንድ ፡ በንድ ፡ በተራ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ለመሆን ፡ መፈለጋቸውን ፡ የሚያረጋግጡበትን ፡ ቃል ፡ ይቀበላል ። ማረጋገጫ ፡ ቃሉን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ በሕግ ፡ ስም ፡ ሁለቱንም ፡ አበሮች ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ብሎ ፡ ይለፍፋል ፡ (ቊጥር ፡ ፮፻፬) ።

ሁለት ፡ ሰዎች ፡ በብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፡ ሊተሳሰሩ ፡ ሲያቅዱ ፡ እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ የታቀደው ፡ ጋብቻ ፡ ከሚከበርበት ፡ ዕለት ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ አስቀድመው ፡ ስለዕቅዳቸው ፡ ለሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ ማስታወቅ ፡ አለባቸው ፡ (ቊጥር ፡ ፭፻፺፱) ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙን ፡ ጋብቻው ፡ እንዳይፈጸም ፡ የሚያደናቅፍ ፡ ምክንያት ፡ የደረሰው ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ጋብቻው ፡ እንዳይፈጸም ፡ የሚያግድ ፡ ምክንያት ፡ መኖሩን ፡ ራሱ ፡ ለማመኑ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ያለው ፡ እንደሆነ ፡ ጋብቻውን ፡ ከመሾም ፡ መታገዱ ፡ ግዴታው ፡ ነው ፤ ጋብቻቸውን ፡ በመሾሙ ፡ ያገዱትን ፡ ምክንያቶችም ፡ ወደፊት ፡ ለሚአብሩት ፡ መሳዮች ፡ ያስታውቃል ፡ (ቊጥር ፡ ፮፻፯) ። የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ ጋብቻውን ፡ ስላገደባቸው ፡ በሁለቱ ፡ አበሮች ፡ ማነኛውም ፡ አንዱ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይግባኝ ፡ ሊል ፡ ይችላል ፤ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ክልከላው ፡ ትክክለኛ ፡ አለመሆኑን ፡ የደረሰበት ፡ እንደሆነ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ ጋብቻቸውን ፡ እንዲሾም ፡ ይገደዳል ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደዚህ ፡ በበየነ ፡ ጊዜ ፡ ሹሙ ፡ በማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ምክንያት ፡ አሳቦ ፡ ጋብቻው ፡ እንዳይፈጸም ፡ ሊከለክል ፡ አይችልም ፡ (ቊጥር ፡ ፮፻፰) ።

የሃይማኖት ፡ ጋብቻ ፡ የሚከበረው ፡ የበለ ፡ ጉዳይ ፡ ወገኖቹ ፡ ሃይማኖት ፡ ከደነበው ፡ ሥርዓቶች ፡ ጋራ ፡ በሚስማማ ፡ መልክ ፡ ነው ። የሃይማኖት ፡ ጋብቻዎች ፡ እንደሌላው ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻ ፡ ሁሉ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ በሁሉ ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻዎች ፡ የውል ፡ የጋራ ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚዳኙ ፡ ናቸው ፤ እንዲሁም ፡ ጋብቻው ፡ የተነገረበት ፡ ሃይማኖት ፡ ላዘዛቸው ፡ ግዴታዎችም ፡ ተጠያቂ ፡ ናቸው ።

ለልማድ ፡ ጋብቻ ፡ የሚሆኑት ፡ ሥርዓቶች ፡ ዕቅድ ፡ አበሮቹ ፡ የሚኖሩበት ፡ ወይም ፡ ከነሱ ፡ አንዱ ፡ በሚኖርበት ፡ ነገድ ፡ ደንቦች ፡ የታዘዙት ፡ ናቸው ። በዚህም ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻ ፡ ቢሆን ፡ በሕጉ ፡ የሠፈሩትን ፡ ግዴታዎች ፡ የነገዱ ፡ ልማድ ፡ ቢቀበለው ፡ በይ

ቀበለውም ፡ ለሁሉ ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ የተደነገጉት ፡ የወል ፡ የጋራ ፡ ግዴታዎች ፡ በሙሉ ፡ እንዲጠበቁ ፡ ይገባል ።

የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ ማስታወሻዎች ፡ (ማለት ፡ የተወለዱትን ፡ የተጋቡትንና ፡ የሞቱትን ፡ መመዝገቢያ ፡ ) በተቋቋመ ፡ ጊዜ ፡ ጋብቻን ፡ የሚያፈጽመው ፡ ሰው ፡ ጋብቻውን ፡ በማስታወሻ ፡ እንዲመዘግበው ፡ ይገደዳል ፡ እንዲሁም ፡ ማስታወሻው ፡ በሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ ማስታወሻ ፡ መዝገቦች ፡ ይመዘገባል ። እንግዲህ ፡ ለጋብቻው ፡ ማስረጃ ፡ ምስክር ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ፡ ከእንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ማስታወሻ ፡ መዛግብት ፡ የተውጣጣ ፡ ቅጅን ፡ ሲያቀርቡ ፡ ነው ፡

<u>፫ ፡ ለሁሉ ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ ግዴታዎች ፡ ስለማስከበር ፡ የተወሰኑ ፡ ድንጋጌዎች ፡</u>

<u>ወይም ፡ ምጽዋኑ ፡ ግዴታዎች ፡ የሆኑ ፡ ሕጎች ፡</u>

የጋብቻዎችን ፡ ግዴታዎች ፡ ከወሰነ ፡ በኋላ ፡ እሊሁ ፡ ግዴታዎች ፡ ባይጠበቁ ፡ የሚያስከትሉትን ፡ ቅጣቶች ፡ የሚወስኑ ፡ ድንጋጌዎችን ፡ ሕጉ ፡ ያግጋል ። እሊሀ ፡ ድንጋጌዎችም ፡ የሚመለከቱት—

ሀ. በዕድሜ ፡ የሥጋ ፡ ዝምድናንና ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድናን ፡ ባለ ፡ የቀድሞ ፡ ጋብቻ ፡ ውል ፡ መቀየድ ፡ ያለ ፡ እክል ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ የተወሰነ ፡ ሰው ፡ ለማግባት ፡ አስፈላጊው ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ ባሏ ፡ በሞተባት ፡ የመበለትነት ፡ ጊዜ ፡ ምክንያት ፡ የተነሣ ፡ ዕንቅፋት ፡ እያለ ፡ የተዋዋሉትን ፡ ጋብቻ ፡ ጉዳዮችን ፡ እና ፡

ለ/ በኃይል ፡ አስገዳጅነት ፡ ወይም ፡ በሀላዌ ፡ ዝንጋታ ፡ ፈቃደኝነት ፡ ተጓድሎ ፡ ሳለ ፡ የተዋዋሉትን ፡ ጋብቻ ፡ ጉዳዮች ፡ ነው ።

"ሀ"ን ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ በሕግ ፡ የታገጉት ፡ ድንጋጌዎች ፡ የሚከተሉትን ፡ ይከታል—

(፩ ፤) ጋብቻውን ፡ የሾመው ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ባለሥልጣን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ እንዲቀጣና ፡ ጥምሮቹ ፡ ራሣቸው ፡ ምስክሮቹና ፡ የጋብቻን ፡ በዓል ፡ ለመሾም ፡ ተከፋይ ፡ የሆኑትን ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ እንዲቀጡ ፡ እና ፡

(፪ ፤) ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ (ዋጋ ፡ አልባ ፡ እንዲሆን ፡ ) ነው ።

"ለ"ን ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ (ዋጋ ፡ አልባ ፡ እንዲሆን ፡ ) ያግጋል ።

## በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ በቅጣት ፡ ላይ ፡ መውደቅ።

የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ባለሥልጣን ፡ ለጋብቻው፡

ሀ/ በዕድሜ ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፯ ፡)

ለ/ በጋብቻ ፡ ወይም ፡ በሥጋ ፡ ዝምድና ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፲ ፡)

ሐ/ ቀድሞ ፡ የነበረበት ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ እስካሁን ፡ በማለቱ ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፲፩ ፡)

መ/ ለማግባት ፡ አስፈላጊውን ፡ ሥልጣን ፡ በጣ ፡ ኢ.ስኪ.ል ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፲፬ ፡)

ሠ/ ለማግባት ፡ ፈቃደኝነቱ ፡ በኃይል ፡ አስገዳጅነት ፡ የተገኘ ፡ በመሆኑ ፡ ከመ ኅደሉ ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፲፭ ፡ (፪) ፡) ምክንያት ፡ እንቅፋት ፡ መኖሩን ፡ ሲያ ውቅ ፡ ወይም ፡ ሊያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ሲገባው ፡ (ማለት ፡ ንቁ ፡ የሕዝብ ፡ አገ ልጋይ ፡ ሊያደርገው ፡ የሚገባውን ፡ የመጠያየቅ ፡ ተግባር ፡ ካከናወነ ፡ በኋላ ፡) ጋብቻን ፡ አፈጣጥሞ ፡ ቢገኝ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ ቅጣት ፡ ያገኘዋል ።

ደግሞም ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ በጋብቻው ፡ ላይ ፡ የቀረበን ፡ መቃወሚያ ፡ ቍጥር ፡ ፮፻፲፱፡ ወይም ፡ ባኋ ፡ ሞቶበት ፡ የመበለትነት ፡ ጊዜን ፡ ባለመፈጸሟ ፡ ( ቍጥር ፡ ፮፻፹ ፡ ) እንቅ ፋት ፡ እያለ ፡ ጋብቻውን ፡ የለፈፈ ፡ ሹሙን ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣኑን ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ ቅጣት ፡ ይደርስበታል ። ሹሙ ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣኑ ፡ እን ዲያውቅ ፡ ወይም ፡ ሊያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ይገባው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ስለሚለው ፡ ሁለት ፡ ምሳሌዎች ፡ ሹሙ ፡ ፈልጐ ፡ ቢደርስበት ፡ ባይደርስበት ፡ የሹሙ ፡ ፈንታ ፡ እንጂ ፡ ሕጉ ፡ የሚቸገርበት ፡ ጉዳይ ፡ እንዳላደረገው ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ፡ ምክንያቱም ፡ ስለጋብቻው ፡ ተገቢ ፡ መቃወሚያ ፡ ቀርቦ ፡ ኑሮ ፡ እንደሆነ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ መቃወሚያ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የታወቀ ፡ በግልጽ ፡ የሚቀርብ ፡ ነው ፤ ስለባኋ ፡ የሞተበት ፡ የመበለትነት ፡ ጊዜም ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋምን ፡ መመዝገቢያ ፡ ማስታወሻዎችን ፡ የመሰሉ ፡ መዛግ ብቶች ፡ ከተቋቋሙ ፡ ከማስታወሻዎቹ ፡ ጋራ ፡ የማስተያየትን ፡ ተግባር ፡ የሚመለከት ፡ ነው።

እንዲሁም ፡ ከላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ የጋብቻ ፡ አጋጅ ፡ እንቅፋቶች ፡ ማናቸውም ፡ አንዱ ፡ እያለ ፡ ጋብቻ ፡ ታውጆ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ በአበሮቹ ፡ ራሳቸው ፡ ጋብቻውን ፡ በመረቁ ፡ ሰዎችና ፡ በጋብቻው ፡ ምስክሮች ፡ በነበሩት ፡ ላይ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ ቅጣት ፡ ይደርስባቸዋል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከሚጋቡት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ከሚፈለገው ፡ ዕድሜ ፡ በታች ፡ በሆነበት ፡ ጋብቻ ፡ ጉዳይ ፡ ቅጣት ፡ የሚደርስበት ፡ በዚያው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ነው ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፯ ፡ (፪) ፡) ። ከሚጋቡት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ አንዱ ፡ ኢ.ስኪ.ል ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ ያለ ፡ በመሆኑና ፡ አስፈላጊው ፡ የማግቢያ ፡ ሥልጣን ፡ ፈቃድ ፡ በሌለበት ፡ ጋብ ቻ ፡ ጉዳይ ፡ ተቀጭው ፡ ሌላው ፡ የጋብቻው ፡ ወገን ፡ ነው ፤ (ጥር ፡ ፮፻፲፬ ፡ (፪) ።) በወ ንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጉ ፡ ቍጥር ፡ ፮፻፲፭ ፡ እና ፡ ፬፻፲፪ ፡ በተከታታዮቹም ፡ በሕግ ፡ የተ ከለከለን ፡ ጋብቻ ፡ ያወጀ ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ ባለሥልጣን ፡ የሚቀጣበት ፡ ድንጋጌ ፡ ሲኖር ፡ አበሮቹ ፡ ጋብቻ ፡ ፈቅደው ፡ የመረቁ ፡ ሰዎችና ፡ ምስክሮቹ ፡ የሚቀጡበት ፡ ድንጋጌ ፡

አለመመደቡን ፡ መገንዘብ ፡ ያሻል ። ዋጋ ፡ ባለው ፡ ጋብቻ ፡ ውል ፡ እንደተያዘ ፡ የመዠመሪያው ፡ ኅብረት ፡ ከመፍረሱ ፡ ወይም ፡ ውድቅ ፡ ከመሆኑ ፡ በፊት ፡ ሥራዬ ፡ ብሎ ፡ አልሞ ፡ ሌላ ፡ ጋብቻ ፡ የተዋዋለ ፡ አበር ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ ጥንድ ፡ ጋብቻ ፡ ስለፈጸመ ፡ ቅጣት ፡ እንዲያገኘው ፡ ተደርጓል ፡ (ቊጥር ፡ ፮፻፲፮ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ።) ደግሞም ፡ ለጋብቻው ፡ ፈቃደኝነትን ፡ ለማግኘት ፡ ሌላ ፡ ሰውን ፡ በኃይል ፡ ያስገደደ ፡ ሰውም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጉ ፡ ቊጥር ፡ ፮፻፲፮ ፡ ይቀጣል ፤ (እንዲሁም ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቊጥር ፡ ፭፻፳፫ ፡ ይመለከቷል ።)

## ስለጋብቻው ፡ መፍረስ ፡ ዋጋ ፡ አልጋ ፡ መሆን ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፡ (ማዕቀበ ፡) የምጥንታ / (ምጽዋን ፡ ድንጋጌዎች ፡ ማለቱ ፡ በተሻለ)

ጋብቻው ፡ የሚፈርስበትን ፡ (ዋጋ ፡ አልባ ፡ የሚሆንበትን) የሚከተው ፡ ሌላው ፡ ሕግ ፡ ውጤትን ፡ የሚያገኘው ፡ በሚከተሉት ፡ መንገዶች ፡ ነው ።

ሀ/ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ከዚህ ፡ ግርጌ ፡ ጥያቄን ፡ ሊያቀርቡ ፡ ይገባቸዋል ፡ ተብሎ ፡ በተጠቀሱት ፡ ሰዎች ፡ ጥያቄው ፡ ቀርቦለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካላዘዘ ፡ በስተቀር ፡ ጋብቻው ፡ አይፈርስም ። (ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ያመለከቷል ፡ እንጂ ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ገላጋዮች ፡ አለመሆኑን ፡ ይገነዘቧል ፤ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ የሚያዩት ፡ የፍቺን ፡ ጥያቄዎች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በጋብቻ ፡ ግዴታዎች ፡ መጣስ ፡ በማዕቅብ ፡ ሕግ ፡ ምጥንታ ፡ የሚፈርሰውን ፡ ጋብቻ ፡ አይደለም)፤

ለ/ ከተዋዋይ ፡ ወገኖቹ ፡ አንዱ ፡ ከሚፈለገው ፡ ዕድሜ ፡ በታች ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ወይም ፡ የሥጋ ፡ ዝምድና ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድና ፡ መተሳሰሪያ ፡ ከመኖሩ ፡ የተነሣ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ በማነኛው ፡ ጉዳዩ ፡ ነው ፡ ባይ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ በዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጥያቄ ፡ ሊቀርብ ፡ ይችላል ፤ እንዲህ ፡ ያለው ፡ አቤቱታ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጋብቻው ፡ ይፈርስ ፡ ዘንድ ፡ እንዲፈቅድ ፡ ይገባዋል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ፍርሻው በጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ ከሚፈለግበት ፡ ዕድሜ ፡ በታች ፡ ኑሮ ፡ አሁን ፡ ከሚፈለገው ፡ ዕድሜ ፡ በደረሰው ፡ መሰይ ፡ ላይ ፡ አይጸናም ። (ቊጥር ፡ ፮፻፴)፤

ሐ/ ከጥንድ ፡ ጋብቻ ፡ የተነሣ ፡ ጋብቻው ፡ ፍርስ ፡ እንዲሆን ፡ በጥንዱ ፡ ጋብቻ ፡ ከአበሩት ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ፤ ግን ፤ ሁለተኛው ፡ ጋብቻው ፡ በሚነገርበት ፡ ጊዜ ፡ የቀድሞው ፡ ጋብቻው ፡ አበር ፡ በሕይወት ፡ መኖሩ ፡ በፍጹም ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ጋብቻው ፡ ፍርስ ፡ እንዲሆን ፡ አይበይንም ፤ (ቊጥር ፡ ፮፻፲፪) ። የቀድሞው ፡ ጋብቻው ፡ አበር ፡ እንደሞተ ፡ መታወቁ ፡ ሲመሠረት ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ ጋብቻ ፡ የነበረው ፡ ወዲያውኑ ፡ ባለ ፡ ዋጋ ፡ ይሆናል ፤ እንዲሁም ፡ ከጥንዱ ፡ (ከተደረበበት ፡) ጋብቻ ፡ የተነሣ ፡ ፍርስ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ አይቻልም ፤

መ/ ያለአክል ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ የተወሰነ ፡ ሰው ፡ (ዕክቡ) እንዲያገባ ፡ ሥልጣን ፡ ከማጣቱ ፡ የተነሣ ፡ ጋብቻ ፡ ፍርስ ፡ እንዲሆን ፡ ያለአክሉ ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ዕክቡ ፡ (በፍርድ ፡ የተወሰነው ፡ ሰው) ራሱ ፡ ወይም ፡ ኢአኪሉ ፡ ጋብቻ ፡ ሊመርቅ ፡ ሊፈቅድ ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፤

ሠ/ ወይም ፡ የመበለትነት ፡ ዕድሜ ፡ ከለመጠበቁ ፡ ብቻ ፡ የተነሣ ፡ (ቁጥር ፮፻፳(፫)፥ ወይም ፡ ተደርጐ ፡ ለነበረው ፡ መቃወሚያ ፡ ምንም ፡ ግምት ፡ አልተሰጠውም ፡ ከማለት ፡ ብቻ ፡ የተነሣ ፡ ጋብቻው ፡ ፈራሽ ፡ እንዲሆን ፡ ጥያቄ ፡ ለማድረግ ፡ አይቻልም ፤ እነሆ ፡ ለምሳሌ ፡ የዝምድና ፡ መተሳሰሪያ ፡ በእውነቱ ፡ ሳይኖር ፡ በወደፊቱ ፡ ሙሰዮች ፡ መካከል ፡ ዝምድና ፡ አለ ፡ ከማለት ፡ የተነሣ ፡ ጋብቻው ፡ እንዳይሾም ፡ መቃወሚያ ፡ ቀርቦ ፡ ኑሮ ፡ እንደሆነ ፡ እንግዲህ ፡ ለማገጃ ፡ ምክንያቱ ፡ ምንም ፡ ግምት ፡ ሳይሰጠው ፡ በመቅረቱ ፡ ጋብቻውን ፡ ለማፍረስ ፡ በቂ ፡ መነሻ ፡ ምክንያት ፡ አይሆንም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በእውነቱ ፡ የዝምድና ፡ መተሳሰሪያ ፡ ካለ ፡ እንግዲያስ ፡ ለመፍረሱ ፡ አይነተኛ ፡ መነሻ ፡ ምክንያት ፡ የሚሆነው ፡ ይህ ፡ መተሳሰሪያ ፡ ነው ።

ለጋብቻው ፡ በኃይል ፡ አስገዳጅነት ፡ የተተፋ ፡ ወይም ፡ በሕላዊ ፡ መሳሳት ፡ የተገኘ ፡ የደፈረሰ ፡ ፈቃደኝነት ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ እንዲፈርስለት ፡ አቤቱታ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ አስገዳጅ ፡ ኃይል ፡ ወይም ፡ መሳሳቱ ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ አቤቱታም ፡ ያስገደደው ፡ ኃይል ፡ ከተቋረጠበት ፡ ወይም ፡ ስሕተቱን ፡ ከተረዳበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ በስድስት ፡ ወሮች ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ። በማናቸውም ፡ መንገድ ፡ ቢሆንም ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ የሚደረገው ፡ ጥያቄ ፡ ጋብቻው ፡ ከተከበረበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ሊቀርብ ፡ አይችልም ፤ (ቁጥር ፡ ፮፻፲፯ ፡ እና ፡ ፮፻፲፰) ።

## ለልዩ ፡ ልዩ ፡ የጋብቾች ፡ ዓይነቶች ፡ የሚያገለግሉ ፡ ልዩ ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፤

## («የምጥንታ ፡ ሕጎች ፡/ ድንጋጌዎች ፡» ምባልከፋ ፡)

እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የታተቱት ፡ የቅጣት ፡ ሕጎች ፡ ድንጋጌዎች ፡ ለሁሉም ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ የሚሆኑትን ፡ የወል ፡ ግዴታዎች ፡ የሚመለከቱ ፡ ናቸው ፤ ግን ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ በተለይ ፡ የተመደቡ ፡ ሌሎች ፡ የምጥንታ ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፡ አሉ ። የብሔራዊ ፡ ጋብቻ ፡ ልዩ ፡ የቅጣት ፡ ሕጐች ፡ የሚመለከቱት ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ የመዛግብት ፡ ሹሙንና ፡ ተጣማሪዎቹንና ፡ ምስክሮቹንም ፡ ነው ፤ በምንም ፡ ጉዳይ ፡ ቢሆን ፡ እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ የቅጣት ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጋብቻውን ፡ የሚያፈርስ ፡ ውጤትን ፡ አይወልዱም ። በዚያው ፡ ሥፍራ ፡ የስድስት ፡ ወር ፡ የመኖሩ ፡ ጊዜ ፡ ግዴታ ፡ ሳይከበር ፡ ጋብቻን ፡ ያወጀ ፡ የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹም ፡ <u>እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ግዴታ ፡ አለመጠበቁን ፡ እያወቀ ፤ ወይም ፡ ሊያውቅ ፡ ሲገባው ፤)</u> በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የሚቀጣ ፡ ነው ፤ ደግሞም ፡ ተጣማሮቹና ፡ ምስክሮቹ ፡ ቅጣት ፡ ይገባቸዋል ። የሕዝብ ፡ የክብር ፡ አቋም ፡ መዛግብት ፡ ሹሙ ፡ ጋብቻውን ፡ በሚያስከብርበት ፡ ጊዜ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፫ ፡ የተመለከተውን ፡ የማስታወቂያ ፡ ግዳጅ ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፬ ፡ እንደ ፡ ተመለከቱ ፡ ሥርዓቶች ፡ አበሮቹና ፡ ምስክሮቹ ፡ ስለሚቀበሉት ፡ መሐላና ፡ የመሰዮቹን ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ለመሆን ፡ መፈለጋቸውን ፡ ማረጋገጫ ፡ መቀበል ፡ ሁሉ ፡ ሳይጠብቅ ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጉ ፡ ቅጣት ፡ ይገባዋል ።

በሃይማኖት ፡ ወይም ፡ በልማድ ፡ ጋብቻ ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ማናቸውም ፡ ሥርዓቶች ፡ ሳይጠበቁ ፡ ቀሩ ፡ በማለት ፡ ጋብቻውን ፡ ለመሻርና ፡ ለማፍለስ ፡ መነሾ ፡ ምክን

ያት ፡ አይደለም ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣን ፡ የሃይማኖት ፡ ጋብቻን ፡ ሲሽረው ፡ እንደ ፡ ፍቺ ፡ ምክንያት ፡ ሊቆጠር ፡ ይችላል ፡ (ቁጥር ፡ ፩፻፹፫ ፡ (፪ ፡) እና ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፹፬ ።) የልማድ ፡ ጋብቻ ፡ በነገድ ፡ የልማድ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መሻር ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የሕግ ፡ ውጤት ፡ የሚያስገኝ ፡ አይደለም ። በሃይማኖትና ፡ በልማድ ፡ ጋብቻዎች ፡ ግዴታዎቹና ፡ ሥነሥርዓቶቹ ፡ ባለመጠበቃቸው ፡ የሚጣለው ፡ መቀጫ ፡ ጋብቻውን ፡ በሾመው ፡ ባለሥልጣን ፡ ላይ ፡ የዚያ ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ ነገድ ፡ ወግና ፡ ልማድ ፡ የወሰነውን ፡ የገንዘብ ፡ ቅጣት ፡ ብቻ ፡ መክፈልና ፡ የተበደለው ፡ ወገን ፡ ኪሣራ ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ማስቻል ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ያን ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ የልማድ ፡ ወግ ፡ ቸላ ፡ በማለት ፡ (<u>በዚያ ፡ ሃይማኖት ፡ ወይም ፡ ልማድ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ተቃራኒ ፡ ልማድ ፡ ቢኖር ፡ ባይኖርም ፡</u>) እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ሲሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቅጣቱንና ፡ የኪሣራ ፡ ገንዘብ ፡ መጠኑን ፡ ለማውረድ ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ቅጣትና ፡ የጉዳት ፡ ካሣ ፡ የወጣበት ፡ ወግና ፡ ልማድ ፡ አእምሮ ፡ ሊረዳቸው ፡ የማይችል ፡ ወይም ፡ ለርትዕና ፡ ለበጐ ፡ ምግባር ፡ ጠባይ ፡ (ሞራሊቲ ፡) ተቃራኒ ፡ መስሎ ፡ ከታየው ፡ ልማዱ ፡ ውጤት ፡ እንዳያገኝ ፡ ለመከልከል ፡ ይችላል ፡ (ቁጥር ፡ ፩፻፹፭ ።)

## ፬ ፤ የጋብቻ ፡ ውጤቶች ።

ጋብቻ ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ውጤት ፡ መልከች ፡ ሁለት ፡ ናቸው ፤

ሀ/ በግላዊ ፡ የተለየ ፡ ዝምድናቸው ፤

ለ/ በገንዘባቸው ፡ ነው ።

ጋብቻ ፡ በግላዊ ፡ የተለየ ፡ አቋማቸው ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤቶች ፡ የሚመለከቱት ፡ በአበሮቹ ፡ መከከል ፡ የሚያመጣውን ፡ ግላዊ ፡ ልዩ ፡ ዝምድና ፡ ነው ፤ በገንዘባቸው ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤቶች ፡ የሚመለከቱት ፡ እያንዳንዱ ፡ የግል ፡ የሆኑትንና ፡ የሁለቱ ፡ አበሮች ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረት ፡ የሆኑትን ፡ ነው ። ጋብቻ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ ብሔራዊ ፡ ሃይማኖትና ፡ ልማድ ፡ ጋብቻ ፡ ብሎ ፡ ሳይለይ ፡ በሁሉም ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ ያው ፡ አንድ ፡ ነው ፡ (ቁጥር ፡ ፩፻፹፮ ።) የሩካቤ ፡ ሥጋው ፡ ተግባር ፡ ቢፈጸም ፡ ባይፈጸምም ፡ ጋብቻው ፡ ውል ፡ እንደገቡ ፡ ወዲያውኑ ፡ ውጤቶቹን ፡ ያስከትላል ።

## የ ጋ ብ ቻ ፡ ው ል ።

ጋብቻው ፡ ከመሾሙ ፡ በፊት ፡ እጮኞቹ ፡ ጋብቻቸው ፡ በሀብትና ፡ ንብረታቸው ፡ በኩል ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ የሚያስተዳድር ፡ ውል ፡ ሊፈጽሙ ፡ ይችላሉ ፡ ደግሞም ፡ በነዚያ ፡ ሕጉ ፡ ባልከላከላቸው ፡ ማናቸው ፡ ይዞታዎች ፡ ላይ ፡ ጋብቻቸው ፡ በመከከላቸው ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ልዩ ፡ የግል ፡ ግንኙነት ፡ ስለሚመለከቱት ፡ የመተዳደሪያ ፡ ስምምነቶችን ፡ በውሉ ፡ ላይ ፡ ሊያሰፍሩ ፡ ይችላሉ ። የጋብቻ ፡ ውሉ ፡ በወደፊት ፡ አበሮቹ ፡ የተፈረመ ፡ ጽሑፍ ፡ መሆን ፡ ይገበዋል ፤ አራት ፡ ምስክሮችም ፡ (ሁለት ፡ በባልዮው ፤

በኩል ፡ ሁለት ፡ በሚስቲት ፡ በኩል ፤) እንዲገኙ ፡ ያስፈልጋል ፤ እሊህን ፡ የውል ፡ ቅጦች ፡ ከጣሰ ፡ የጋብቻ ፡ ውሉ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ውጤት ፡ የለውም ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፴፱ ።) ከሚዳሩት ፡ አንዱ ፡ ኢ.አኪ.ል ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ የተወሰነ ፡ ሰው ፡ (ሰክብ ፡ ) ሲሆን ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፴፯ ፡ የተመለከቱ ፡ የሚከተሉት ፡ ተፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ይጠበቃሉ ፤

ሀ) ኢ.አኪ.ልን ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ ከራሱ ፡ ከኢ.አኪ.ሉ ፡ ፈቃደኝነት ፡ በላይ የሞግዚቱ ፡ ምረቃ ፡ ( ፈቃድ ፡ ) አስፈላጊ ፡ ነው ፤

ለ) በፍርድ ፡ የታገደ ፡ ሰውን ፡ በሚመለከተው ፡ ጉዳይ ፡ የጋብቻ ፡ ውሉ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ የጸደቀ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ።

የጋብቻ ፡ ውልን ፡ ነክ ፡ በሆኑ ፡ ጉዳዮች ፡ በፍርድ ፡ የታገደን ፡ ሰው ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ እንዳይፈጽም ፡ የማያስችለው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ከላይ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፴፱ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሥርዓቶች ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ ሳይፈጽም ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ውል ፡ ራሱ ፡ ሊያከናውን ፡ ይችላል ።

በቍጥር ፡ ፮፻፵ ፡ መሠረት ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ከተሰናዳ ፡ በኋላ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ወይም ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ ካለው ፡ ሰው ፡ ( ኖታሪ ፡ ) ዘንድ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ይገባል ፡ እንዲሁም ፡ ከአበሮቹ ፡ ማንኛውም ፡ መሳይ ፡ ወይም ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የፈቀደለት ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ከውሉ ፡ ለማድረስና ፡ አገላብጦ ፡ ለመመርመር ፡ ይቻለዋል ። ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ጋራ ፡ በንድ ፡ ነገር ፡ የሚስማማ ፡ ሰው ፡ ጋብቻው ፡ በሀብታቸውና ፡ ንብረታቸው ፡ ላይ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ አበሮቹ ፡ የተስማሙትን ፡ መረዳቱ ፡ አውራ ፡ ጉዳዩ ፡ ነው ፡ ስለምን ፡ ቢሉ ፡ ላንዳንድ ፡ ፍርድ ፡ ነክ ፡ ድርጊቶች ፡ የጥንዱ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ መስማማት ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ፡ ይኋል ።

የጋብቻ ፡ ውል ፡ ከተዘጋጀ ፡ በኋላ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ አንዳንድ ፡ ጉዳዮች ፡ እንዲሻሻል ፡ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ጥቅም ፡ የሚጠይቅ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ አበሮቹ ፡ በጠየቁት ፡ መሠረት ፡ በቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ ( የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ) አማካይነት ፡ ማናቸውም ፡ ልውውጥ ፡ ሊከናወን ፡ ይቻላል ፤ እንግዲህ ፡ የመዠመሪያውን ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ የሚመረምር ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የተከናወነውን ፡ መሻሻል ፡ ይገነዘበው ፡ ዘንድ ፡ በውሉ ፡ ውስጥ ፡ የተፈጸመው ፡ ማናቸው ፡ ልውውጥ ፡ ትክክለኛ ፡ ቅጂ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ወይም ፡ ለማዋዋል ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ይቀመጣል ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፵፪ ።) ከጋብቻው ፡ በፊት ፡ ምንም ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ስላላሰናዱና ፡ ባልና ፡ ሚስቱ ፡ በጋብቻ ፡ ዘመናቸው ፡ ውስጥ ፡ ውል ፡ ሊገቡ ፡ ቢሹ ፡ በቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ካልተፈቀደ ፡ በቀር ፡ ውሉ ፡ አንዳችም ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ውጤትን ፡ አያገኝም ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፵፫ ።) ከጋብቻው ፡ በፊት ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ በጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የጋብቻው ፡ ውል ፡ ባልተደረገበት ፡ ሁኔታ ፡ ሁሉ ፡ ጋብቻው ፡ በግላዊ ፡ የተለየ ፡ ዝምድናና ፡ በሀብት — ንብረት ፡ የሚያስከትላቸው ፡ ውጤቶች ፡ በሕጉ ፡ በተወሰኑት ፡ አንቀጾች ፡ መሠረት ፡ ይዳኛሉ ። የጋብቻ ፡ ውል ፡ የአበሮቹን ፡ የተለየ ፡ ግላዊ ፡ ግንኙቶችንና ፡ የሀብቶቻቸው ፡ ጉዳዮች ፡ እንዴት ፡ እንደሚተዳደሩ ፡ ከለል ፡ አድርጐ ፡ መደርደር ፡ ይገባዋል ፤ እንዲያው ፡ በቀላሉ ፡ ሁሉንም ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ወግና ፡ ልማድ ፡ በመወርወር ፡ ፍላጐቶቻቸው ፡ ሊብራሩ ፡ አይችሉም ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፵፭።) በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ የስምምነቶቹ ፡ ስልቶች ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጠቅላላ ፡ መልክ ፡ ተመርተው ፡ እንደሆነ ፡ በሁለቱም ፡ በልዩው ፡ ግላዊ ፡ ዝምድናና ፡ በሀብታቸው ፡ ረገድ ፡ ጋብ

ቻው ፣ የሚያስከትላቸው ፣ ውጤቶች ፣ በሕጉ ፣ በሰፈሩት ፣ ድንጋጌ ፣ አንቀጾች ፣ ይዳ ኛሉ ። የጋብቻ ፣ ውል ፣ በተጋቢዎቹ ፣ መካከል ፣ የሚዘጋጅ ፣ ውል ፣ ስለሆነ ፣ ሦስተኛ ፣ ወገኖችን ፣ ነክ ፣ የሆነ ፣ የውለታ ፣ አንቀጾች ፣ ሊይዝ ፣ አይችልም ። እንዲሁም ፣ የጋብ ቻ ፣ ውል ፣ በሕጉ ፣ መሠረት ፣ አዛዥ ፣ የሆኑትን ፣ ድንጋጌዎች ፣ ( ለምሳሌ ፣ የአበሮቹ ፣ እርስ ፣ በራሳቸው ፣ መከባበርን ፣ መደጋገፍንና ፣ መረዳዳትን ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፴፮ ፣ ( እና ፣ የአብሮ ፣ መኖር ፣ ግዳጅን ፣ ( ቍጥር ፣ ፮፻፵ ፣ ) ጉዳዮች ፣ ) ተቃራኒ ፣ በሆነ ፣ መልክ ፣ ለማከናወን ፣ አይችልም ።

<u>የጋብቻ ፣ ልዩና ፣ ግላዊ ፣ ውጤቶች ።</u>

ሕጉ ፣ በሚፈቅድላቸው ፣ ጉዳዮች ፣ ላይ ፣ አበሮቹ ፣ በሌላ ፣ መልክ ፣ ካልተስማሙ ፣ በቀር ፣ የጋብቻ ፣ ልዩና ፣ ግላዊ ፣ ውጤቶቹ ፣ የሚከተሉት ፣ ናቸው ፣

ሀ/ ባልየው ፣ የቤተ ፣ ዘመዱ ፣ ጌታ ፣ (ራስ ፣ አውራ) ነውና ፣ ባሏ ፣ በሚያዘት ፣ ሕግን ፣ በዘሉ ፣ ጉዳዮች ፣ ሁሉ ፣ ሚስቲቱ ፣ ለርሱ ፣ የመታዘዝ ፣ ዕዳ ፣ አለባት ፣ ሕጉ ፣ አንዳንድ ፣ መብቶችን ፣ ለሚስቲቱ ፣ ስለሚያዝዝላት ፣ (ለምሳሌ ፣ በቍጥር ፣ ፮፻፴፱ ፣ የግል ፣ ሀብቶቻቸውን ፣ እያንዳንዱ ፣ አበር ፣ እንዲያስተዳድርና ፣ እንዲሸጥ ፣ እንዲለ ውጥ ፣ ወይም ፣ በፈቀደው ፣ መልክ ፣ ከእጁ ፣ ወደ ፣ ሌላ ፣ ሰው ፣ እጅ ፣ እንዲያዘዋውረ ው ፣ በሚፈቅድለት ፣ በመሳሰሉት ፣ ላይ) በሚስቲቱ ፣ እንደዚህ ፣ ያለ ፣ አንዳችም ፣ የመ ታዘዝ ፣ ዕዳ ፣ የማያመጡበት ፣ ነገሮች ፣ አሉ ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፴፭) ። በባልየው ፣ መሪነት ፣ በትክክለኛው ፣ ዘለዓለማዊ ፣ (መንፈሳዊ) በሆነ ፣ ግብርና ፣ በሚጨበጠው ፣ ምድራዊ ፣ ተግባሮች ፣ በኩል ፣ ለመላው ፣ ቤተሰቦቻቸው ፣ እድገት ፣ ሲሉና ፣ ልጆቻቸውን ፣ በሚ ገባ ፣ እኳኋን ፣ ለማሳደግ ፣ ሁለቱም ፣ አበሮች ፣ ለመረዳዳት ፣ የተሳሰሩ ፣ ናቸው ። እንደ ዚሁም ፣ ይህን ፣ ጉዳይ ፣ ነክ ፣ በሆኑት ፣ በጋብቻ ፣ ውሉ ፣ አበሮቹ ፣ የተዋዋሏቸውን ፣ ማናቸውን ፣ ግዴታዎች ፣ ለመፈጸም ፣ የተሳሰሩ ፣ ናቸው ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፴፯) ፤

ለ/ ተመሳዮቹ ፣ ርስ ፣ በራሳቸው ፣ መከባበር ፣ መደጋገፍና ፣ መረዳዳት ፣ አለባቸው ፣

ሐ/ በሕመም ፣ ምክንያት ፣ ወይም ፣ ከሌላ ፣ ምክንያት ፣ የተነሣ ፣ ችሎታን ፣ በማ ጣት ፣ ወይም ፣ ከቤት ፣ በመለየት ፣ ወይም ፣ ከቤተሰብ ፣ በመከብለል ፣ ወይም ፣ ከዚህ ፣ ተመሳሳይ ፣ በሆኑ ፣ ሁኔታዎች ፣ ምክንያት ፣ በቍጥር ፣ ፮፻፴፪ ፣ እንደተመለከተው ፣ ከአ በሮቹ ፣ አንዱ ፣ ቤተ ፣ ዘመዱን ፣ ነክ ፣ የሆኑትን ፣ ግዴታዎች ፣ ለማካሄድ ፣ የተሳነው ፣ እንደሆነ ፣ ግዴታዎቹን ፣ የመፈጸሙ ፣ ተግባር ፣ በሌላው ፣ አበር ፣ ላይ ፣ ይወድቅበ ታል ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፴፰ ፤ ቍጥር ፣ ፯፻፰ ፣ እንዲሁ ፣ ይመለከቷል ፤

መ/ ከአበሮቹ ፣ አንዱ ፣ ከበፊት ፣ ጋብቻ ፣ ልጆች ፣ ቢኖሩት ፣ የእንደዚህ ያሉ ት ፣ ልጆችን ፣ ማስተማር ፣ ነክ ፣ በሆነው ፣ ጉዳይ ፣ መብቱ ፣ በተለይ ፣ የዚያው ፣ የወላ ጁ ፣ ነው ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፴፫) ፤

ሠ አበሮቹ ፣ አንድ ፣ ላይ ፣ ለመኖር ፣ የተሳሰሩ ፣ ናቸው ፣ አድራጐቱ ፣ ለጤንነት ፣ በውል ፣ (በጣም) ጠንቅን ፣ የሚያስከትል ፣ ካልሆነ ፣ በቀር ፣ የጋብቻ ፣ መተሳሰር ፣ የተ ለመደን ፣ ሩካቤ ፣ ሥጋን ፣ ተግባር ፣ ያጠቃልላል ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፵) ፤

ረ/ ባልዮው ፣ የጋራ ፣ መኖሪያ ፣ ሥፍራን ፣ መርጦ ፣ ይመድባል ፣ ነገር ፣ ግን ፣ ባል የው ፣ የመደበው ፣ የጋራ ፣ መኖሪያ ፣ ቦታ ፣ እንዳሻው ፣ በመሆኑ ፣ ከጋብቻው ፣ ውል ፣ አንቀጾች ፣ ጋራ ፣ ተቃራኒ ፣ ሁኖ ፣ ቢገኝ ፣ ሚስቲቱ ፣ ውሳኔውን ፣ በመቃወም ፣ አቤቱታ ዋን ፣ ለቤተዘመዱ ፣ ገላጋዮች ፣ ልታሰማ ፣ ትችላለች ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፵፩) ፤

ሰ/ ምንም ፣ እንኳ ፣ አብሮ ፣ የመኖሮ ፣ ግዴታ ፣ (ይህንንም ፣ በሚቃወም ፣ መልክ ፣ አበሮቹ ፣ በጋብቻ ፣ ውሉ ፣ ከቶ ፣ ሊስማሙ ፣ አይችሉም ፣ ) ቢኖር ፣ ቅሉ ፣ በጋብቻቸው ፣ ዘመን ፣ ውስጥ ፣ አበሮቹ ፣ ልኩ ፣ ለተቆረጠ ፣ ወይም ፣ ላልተቆረጠ ፣ ጊዜ ፣ ተለያይተው ፣ ለመኖር ፣ ሊስማሙ ፣ ይችላሉ ፤ በዚህም ፣ ገጽ ፣ የተፈጸመውን ፣ ስምምነት ፣ ማፍረሱ ፣ በዘፈቀደ ፣ ካልሆነ ፣ በቀር ፤ ከጣምሮቹ ፣ ውስጥ ፣ ማንኛው ፣ በማናቸው ፣ ጊዜ ፣ ተለያ ይቶ ፣ የመኖሩን ፣ ስምምነት ፣ ሊሽረው ፣ ይችላል ። ይህም ፣ ከሃይማኖት ፣ እምነታቸው ፣ የተነሣ ፣ ጋብቻውን ፣ በፍቺ ፣ ለማፍረስ ፣ የተሳናቸው ፣ ሁለት ፣ መሳዮች ፣ ጋብቻው ፣ እንዳለ ፣ ሆኖ ፣ «በገበታና ፣ በምኝታ» በመለያየት ፣ ሊስማሙ ፣ ይችላሉ ። የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕጉ ፣ ፍርዳዊ ፣ መለያየትን ፣ አያስተነትንም ፤ ግን ፣ በለጉዳዮቹ ፣ በስምምነት ፣ መለያየትን ፣ እንዲያገኙ ፣ ያስችላቸዋል ፤

ቀ/ አበሮቹ ፣ ርስ ፣ በራሳቸው ፣ አንዱ ፣ ላንዱ ፣ ታማኝ ፣ ሁኖ ፣ መገኘት ፣ አለባ ቸው ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፵፫) ፤

በ/ ባልየው ፣ ለሚስቱ ፣ ጋሻ ፣ ከለላ ፣ ሁኖ ፣ መጠበቅ ፣ አለበት ፤ ለቤተሰቡ ፣ እድ ገት ፣ ብቻ ፣ እስከሆነ ፣ ድረስ ፣ በግል ፣ ሀብቷና ፣ በጠቅላላ ፣ የጠባይ ፣ ግብሯ ፣ ባልየው ፣ ሚስቲቱን ፣ ሊመራትና ፣ ሊመክራት ፣ ይችላል ፤ በምንም ፣ ምክንያት ፣ ቢሆን ፣ ይህንን ፣ መብቱን ፣ በግል ፣ ያለአገባብ ፣ ወይም ፣ በሚያበሳጫት ፣ መልክ ፣ ሊጠቀምበት ፣ አይች ልም ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፵፬) ፤

ተ/ እያንዳንዱ ፣ አበር ፣ በመረጠው ፣ ሞያና ፣ ተግባር ፣ ሊሰማራ ፣ ይችላል ፣ ሌላ ው ፣ አበር ፣ በዚያ ፣ ሥራና ፣ ተግባር ፣ መዋሉን ፣ ሊቃወም ፣ የሚችለው ፣ የተባለው ፣ ሟያ ፣ ለትዳራቸው ፣ ጥቅም ፣ ተቃራኒ ፣ ሁኖ ፣ ሲገኝ ፣ ብቻ ፣ ነው ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፵፭) ፤ የተጋቡ ፣ ሰዎች ፣ በሥራ ፣ ላይ ፣ መሰማራት ፣ በንግድ ፣ ሕጉ ፣ ከቍ ፣ ፲፮—፳፩ ፣ በተመ ለከተው ፣ ይዳኛል ፤

ቸ/ ለቤታቸው ፣ አገልጋዮችን ፣ ገረድና ፣ አሽከር ፣ ለመቅጠር ፣ የባልየው ፣ አቅ ም ፣ ባልፈቀደለት ፣ ጊዜ ፣ የቤትን ፣ አያያዝ ፣ ተግባር ፣ ግዴታዎችን ፣ ሚስቲቱ ፣ ማከና ወን ፣ አለባት ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፵፮) ።

በአበሮቹ ፣ በጋብቻ ፣ ውሉ ፣ ውስጥ ፣ በሚከተሉት ፣ አንቀጾች ፣ የተዘረዘሩትን ፣ የጋብቻ ፣ ውጤቶቹን ፣ የሚሽር ፣ ስምምነት ፣ ሊገቡ ፣ አይችሉም ፤

(፩) ቍ ፣ ፮፻፴፮ — ስለመከባበር ፣ መደጋገፍና ፣ መረዳዳት ፤

(፪) ቍ ፣ ፮፻፴፯—አንዱ ፣ አበር ፣ ሲደናቀፍ፡ ስለቤተሰቡ ፣ የማስተዳደር ፣ ግዴታዎች ፣ አመራር ፤

(፫) ቍ ፣ ፮፻፴፱ — ከቀድሞ ፣ ጋብቻው ፣ ስላፈራቸው ፣ ልጆች ፣ የተለየ ፣ መብቱ ፤

(፬) ቍጥር ፣ ፮፻፵ — ስለ ፣ አብሮ ፣ መኖር ፤

(፭) ቍጥር ፡ ፯፻፵፫ ስለታማኝነት ፡ (ምንም ፡ እንኳ ፡ አበሮቹ ፡ ከዚህ ፡ ግዴታ ፡ ወደውጭ ፡ ለማፈንገጥ ፡ እንደማይችሉ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ላይ ፡ በነጠረ ፡ መልክ ፡ ጐልቶ ፡ ባይጠቀስ ፡ በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ ለዚህ ፡ ተቃራኒ ፡ በሆነ ፡ መልክ ፡ የተስማሙት ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ውጤት ፡ የማይሰጥ ፡ መሆኑን ፡ ማመን ፡ ይገባል) ።

## <u>ጋብቻ ፡ በገንዘብ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ።</u>

ጋብቻ ፡ በገንዘብ ፡ ላይ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤቶቹ ፡ ሲታይ ፡ አበሮቹ ፡ በተጋቡ ፡ ጊዜ ፡ በነበራቸው ፡ ሀብትና ፡ ከጋብቻው ፡ በኋላ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ባፈሯቸው ፡ ሀብት ፡ መካከል ፡ መለየት ፡ ያስፈልጋል ። በቍጥር ፡ ፯፻፶፫ ፡ መሠረት ፡ መሰዮቹ ፡ ያላቸው ፡ ሀብት ፡ ሁሉ ፡ በምሉ ፡ የጋራ ፡ ማለት ፡ ለሁለቱም ፡ አበሮች ፡ የአንድ ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡ ሀብት ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይገመገማል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከጣምሮቹ ፡ አንዱ ፡ የግል ፡ ሀብቱ ፡ ይኸም ፡ ማለት ፡ የዚያ ፡ ሀብት ፡ ነጠላ ፡ የተለየ ፡ ባለቤት ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ የሚችለው ፡ ይህን ፡ ሐሳብ ፡ ሊያፈርሰው ፡ ይችላል ። ከሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ ጋራ ፡ በማያገናኝ ፡ ነገር ፡ ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ ስለዚህ ፡ ቋሚ ፡ ጉዳይ ፡ አውቆ ፡ ወይም ፡ ሊያውቅ ፡ ዘንድ ፡ በተገባው ፡ ነበረ ፡ የሚባል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የስምምነቱ ፡ ማረፊያ ፡ የሆነው ፡ ሀብት ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ እንጂ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ አለመሆኑ ፡ መረጋገጡ ፡ እንደዚያ ፡ ያሉትን ፡ ሦስተኛ ፡ ወገኖች ፡ የሚነካ ፡ አይደለም ። ለምሳሌ ፡ ሁለት ፡ አበሮች ፡ ጋብቻው ፡ በገንዘባቸው ፡ ላይ ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ አስተዳደር ፡ ወስነው ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ገቡና ፡ እንደዚህ ፡ የመሰለውን ፡ የጋብቻ ፡ ውልም ፡ ከቍጥር ፡ ፯፻፴ ፡ ድንጋጌዎች ፡ ጋራ ፡ በሚስማማ ፡ መልክ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ አስቀመጡ ፡ ተብሎ ፡ ይመሳል ። እንግዲህ ፡ በማናቸውም ፡ አንዱ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ ክለል ፡ ብሎ ፡ እንደተመለከተው ፡ እንደዚያ ፡ ያለው ፡ ሀብት ፡ በእርግጡ ፡ የሚስቲቱ ፡ ግል ፡ ሀብት ፡ ሳለ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ከባልየው ፡ ጋራ ፡ ቢስማማበት ፡ ሦስተኛው ፡ ወገን ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ የተቀመጠውን ፡ የጋብቻ ፡ ውሉን ፡ ቅጅ ፡ በመከታተል ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ መሆኑን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ሲችል ፡ በቸልተኝነቱ ፡ ወዶ ፡ የገባበት ፡ ጣጣ ፡ ስለሆነ ፡ ሚስቲቱ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሀብት ፡ የራሴ ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ መልሳ ፡ ለመጠየቅ ፡ ወይም ፡ ለመውሰድ ፡ መብት ፡ አላት ።

ጋብቻው ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ በሞት ፡ በመለየቱ ፡ ምክንያት ፡ በፍቺ ፡ ወይም ፡ በፍርስ ፡ ምክንያት ፡ እስከተፈጸመ ፡ ድረስና ፡ ሀብቱ ፡ በአበሮቹ ፡ መካከል ፡ ወይም ፡ ሁኔታው ፡ እንደሚያመለክተው ፡ ከመሰዮቹ ፡ በንዱ ፡ ወራሾች ፡ በሌላው ፡ መሰይ ፡ መካከል ፡ እስከሚተነተን ፡ ድረስ ፡ የጋራ ፡ ሀብቱ ፡ ባለቤትነት ፡ የማይከፋፈል ፡ የማይሰነጠቅ ፡ የየአንዳንዳቸው ፡ እኩል ፡ ዕጣ ፡ ያለበት ፡ የሁለቱ ፡ አበሮች ፡ ያንድ ፡ ላይ ፡ ሀብት ፡ እንደሆነ ፡ ይቀራል ። ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ በሞት ፡ በተለየ ፡ ጊዜ ፡ ሌላው ፡ አበር ፡ ከጋራ ፡ ሀብቱ ፡ የሚካፈለው ፡ ድርሻ ፡ (ዕጣ) <u>በወራሽነት ፡</u> ሳይሆን ፡ የጋራው ፡ ሀብት ፡ ተጋሪ ፡ ባለቤትነቱ ፡ የተነሣ ፡ መሆኑን ፡ ደጋግሞና ፡ ለይቶ ፡ መግለጽ ፡ ያሻል ። ከቍጥር ፡ ፯፻፴፫ ፡ በሚስማማ ፡ መልክ ፡ በጋብቻው ፡ ወቅት ፡ በተስማሙበት ፡ ውል ፡ መሠረት ፡ አበሮቹ ፡ ያንድ ፡ ላይ ፡ ሀብቱን ፡ የጋራ ፡ ባለቤትነት ፡ ሊሽሩት ፡ ይችላሉ ። እንዲሁም ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፳ ፡ እንደተመለከተው ፡ አንዳንድ ፡ ዕዳዎች ፡ ማለት ፡ ለአበሮቹ ፡ የትዳር ፡ ጣጣ ፡ ሲባል ፡ የገቡበት ፡ ዕዳዎች ፡ የጋራ ፡ ሀብትን ፡ የሚመለከት ፡ ዕዳ ፡ መሆኑን ፡ መግለጽ ፡ ያስፈልጋል ። ስለዚህ ፡ የጋራ ፡ ሀብቱ ፡ በአበሮቹ ፡ መካከል ፡ በሚተነተንበት ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ዕዳዎች ፡ የጋራ ፡ ንብረቱ ፡ ከሚያወጣው ፡ ዋና ፡ ገንዘብ ፡

ሒሳብ ፡ እንዲነሡ ፡ ይገባል ። ለምሳሌ ፡ የጋብቻ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ባልየው ፡ በየወሩ ፡ የሚያፈራው ፡ ደመወዝ ፡ (በየወሩ ፡ የኢ/ብር ፡ ፮፻ ፡ ይበል) ብቻ ፡ ቢሆንና ፡ ጋብቻው ፡ የቆየው ፡ ለአምስት ፡ ዓመት ፡ እድሜ ፡ (ዋናውን ፡ ገንዘብ ፡ የኢ/ብር ፡ ፴፮ሺ ፡ አድርጎ ፡ ማለት ፡ ነው) ቢሆንና ፡ ለትዳር ፡ ጣጣ ፡ (ለምሳሌ ፡ ለምግብ ፡ ለልብስ ፡ ለልጆች ፡ መማሪያ) በየወሩ ፡ የኢ/ብር ፡ ፭፻ ፡ ይበል ፡ ወጭ ፡ ቢደረግ ፡ ሊተነተን ፡ (ሊከፋፈል) የሚገባው ፡ ያንድ–ላይ ፡ ሀብት ፡ ከኢ/ ብር ፡ ፴፮ሺ ፡ ላይ ፡ የኢ/ብር ፡ ፴ሺ ፡ ተነስቶለት ፡ የኢ/ብር ፡ ፮ሺ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የኢ/ብር ፡ ፴፮ሺ ፡ አይደለም ።

በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ በተቃራኒ ፡ ሌላ ፡ መልክ ፡ ካልተዋዋሉ ፡ በቀር ፡ የግል ፡ ሀብትና ፡ ንብረት ፡ የሚከተሉትን ፡ የከተተ ፡ ነው ፤

ሀ/ በጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ አበር ፡ የነበረውን ፡ ሀብት ፡ ንብረት ፤

ለ/ በጋብቻው ፡ ውስጥ ፡ እያንዳንዱ ፡ አበር ፡ በውርስ ፡ ወይም ፡ በስጦታ ፡ የተቀበለውን ፡ ሀብት ፤

ሐ/ በጋብቻው ፡ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ የግል ፡ ገንዘቡ ፡ በሆነው ፡ ያገኘው ፡ ሀብትን ፡ ወይም ፡ ከአበሮቹ ፡ ያንዱ ፡ የግል ፡ ንብረት ፡ ( ሀብት ፡ )የሆነውን ፡ ባለቤትነት ፡ እጅ ፡ ከማዛወር ፡ በተገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ያገኘው ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ የዚያው ፡ ከአበሮቹ ፡ ያንዱ ፡ የግል ፡ ሁብት ፡ የሆነውን ፡ በማለዋወጥ ፡ ( ልውጫ ፡ ) የተገኘ ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ነው ፤ ይህም ፡ የገባው ፡ በጋብቻው ፡ ወራት ፡ ውስጥ ፡ ስለሆነ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሀብት ፡ የዚያው ፡ የግል ፡ ሀብቱ ፡ ለመሆኑ ፡ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ እንዲያረጋግጡ ፡ ያስፈልጋል ፡ (ይህም ፡ ማረጋገጫ ፡ የሚደረገው ፡ ባለ ፡ ጥቅሙ ፡ አበር ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡) (ቍጥር ፡ ፮፻፵፫ ፡ እና ፡ ፮፻፵፬ ፡ (፪) ) ።

በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ በተቃራኒ ፡ ሌላ ፡ መልክ ፡ ካልተስማሙ ፡ በቀር ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረት ፡ የሚከተሉትን ፡ ያጠቃልላል ፤

ሀ/ የአበሮቹን ፡ ደሞዞችና ፡ ያፈሯቸውን ፡ ገንዘብን ፡ (ጥቅሞችን ፤) እና ፡

ለ/ እያንዳንዱ ፡ አበር ፡ ሊኖረው ፡ ከሚችለው ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ የሚያመጣው ፡ ገቢን ፤ ይኸም ፡ ከአበሮቹ ፡ ያንዱ ፡ የግል ፡ ሀብትና ፡ ንብረት ፡ ከሆነው ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ መሬት ፡ ክራዮች ፡ የሚገኘው ፡ ማለት ፡ ነው ፤ እና ፡

ሐ/ ለሁለቱም ፡ አበሮች ፡ በደፈናው ፡ (አንድ ፡ ላይ ፡ ) በስጦታ ፡ ወይም ፡ በውርስ ፡ የተሰጠውን ፡ ነው ።

የግል ፡ ሀብት ፡ አስተዳደር ፡ ተግባር ፡ ለባለ ፡ ሀብቱ ፡ አበር ፡ ታትቷል ፡ ባለቤቱም ፡ መሳይ ፡ ይህን ፡ ሀብቱን ፡ (እንዳፈቀደው ፡ ሊሸጠው ፡ ሊለውጠው ፡ ሊያዘዋውረው ፡ ወይም ፡ ሊሰጠው ፡ ማለት ፡ ነው ፡) እንዳሻው ፡ ሊያደርገው ፡ ይችላል ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፵፱ ።) ከመሳዮቹ ፡ አንዱ ፡ ያንደኛውን ፡ ( የሌላውን ፡ ) አበር ፡ የግል ፡ ሀብትንና ፡ ንብረትን ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ እንዲያስተዳድርለት ፡ ባልና ፡ ሚስቱን ፡ በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ ከመስማማት ፡ የሚያግዳቸው ፡ ምንም ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ የለም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በሌላ ፡ ተቃራኒ ፡ መልክ ፡ ካልተዋዋሉ ፡ በቀር ፡ ያስተዳደር ፡ የዓመት ፡ ሁኔታ ፡

መግለጫ ፣ ባለቤት ፣ ለሆነው ፣ አበር ፣ እንዲሰጥ ፣ ይገባል ፣ (ቊጥር ፣ ፮፻፶፱)። እንደዚሁም፣ ከአበሮቹ ፣ አንዱ ፣ በግል ፣ ንብረቱ ፣ ላይ ፣ ሌላውን ፣ እሱን ፣ መሰል ፣ እንደራሴው ፣ ሆኖ፣ እንዲሠራ ፣ ሊወክለው ፣ ይችላል ፣ (ቊጥር ፣ ፮፻፶፩ ።)

የጋራ ፣ ሀብት ፣ ንብረትን ፣ ስለማስተዳደር ፣ ጉዳዮች ፤

ሀ/ በደሞዞች ፣ ከግል ፣ ሀብት ፣ ከሚገኙት ፣ ጥቅሞችና ፣ ገቢ ፤ እና ፣

ለ/ ከላይ ፣ ከተመለከቱት ፣ ነገሮች ፣ የተለየ ፣ ሌላ ፣ በሆነው ፣ የጋራ ፣ ሀብት ፣ መካከል ፣ መለየት ፣ ይገባል ።

በመሠረቱ ፣ የጋራ ፣ ሀብቱን ፣ የሚያስተዳድር ፣ ባልዮው ፣ ቢሆን ፣ ቅሉ ፣ ሚስቲቱ፣ የምታፈራውን ፣ ጥቅሞች ፣ ደሞዞችና ፣ ሚስቲቱ ፣ ከግል ፣ ሀብት ፣ ንብረቷ ፣ በምታገኘው ፣ ገቢ ፣ ላይ ፣ ማስተዳደሩ ፣ መብቷ ፣ ስለሆነ፣ የእንደዚህ ፣ ያለውን ፣ ሀብት ፣ ባልየው፣ አያስተዳድርም ፣ (ቊጥር ፣ ፮፻፶፮ ።) ደግሞ ፣ በቊጥር ፣ ፮፻፷፯ ፣ ከተዘረዘሩት ፣ ምክንያቶች ፣ የተነሣ ፣ ባልየው ፣ ለማስተዳደር ፣ ሲሳነው ፣ የጋራ ፣ ሀብት–ንብረትን ፣ በምሉ ፣ ሚስቲቱ ፣ እንድታስተዳድር ፣ ባለመብት ፣ ነች ። ከዚህም ፣ በላይ ፣ ለቤተ ፣ ዘመዱ ፣ ጥቅም ፣ ሲሆን ፤ ለምሳሌ ፣ ለትዳራቸው ፣ እድገት ፣ በሆነ ፣ መልክ ፣ ባልየው ፣ ሀብት–ንብረቱን ፣ ለመመልከት ፣ እንዳልቻለ ፣ ሲረጋገጥ ፣ ወይም ፣ ባልየው ፣ ለትዳሩ ፣ (ለቤተ—ሰቡ ፣ ያለበትን ፣ ግዴታዎች ፣ ቸላ ፣ በማለት ፣ የጋራ ፣ ሀብት ፣ ንብረቱን ፣ ሲሰት—ነው ፣) ሚስቲቱ ፣ የጋራ ፣ ሀብት—ንብረትን ፣ እንድታስተዳድር ፣ የቤተ ፣ ዘመዱ ፣ ገላጋዮች ፣ ሊፈቅዱላት ፣ ይችላሉ ፤ የቤተ ፣ ዘመዱ ፣ ገላጋዮች ፣ እንደዚህ ፣ ሊወስኑ ፣ የሚችሉት ፣ ሚስቲቱ ፣ በጠየቀች ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ (ቊጥር ፣ ፮፻፶፮ ፣ (፫) ።)

እያንዳንዱ ፣ አበር ፣ ጥቅሞቹንና ፣ ደሞዙን ፣ ለመቀበል ፣ እና ፣ ለዚሁ ፣ ጉዳይ ፣ ሲባልና ፣ ደግሞ ፣ ከግል ፣ ሀብት ፣ ንብረቱ ፣ ለሚገባው ፣ ገቢ ፣ መኖሪያ ፣ ይሆነው ፣ ዘንድ ፣ የተለየ ፣ የባንክ ፣ ሂሣብ ፣ ለመክፈት ፣ የመቻል ፣ ባለ ፣ መብት ፣ ነው ፤ ይሁን ፣ እንጂ ፣ ይህ ፣ ሲሆን ፣ ሌላው ፣ አበር ፣ ስለ ፣ ጥቅሞቹ ፣ ሁሉ ፣ ስለደሞዞቹና ፣ ስለ ፣ ተቀበለው ፣ ገቢ ፣ ሁኔታ ፣ ሲጠይቅ ፣ እንዲሰጠው ፣ ግዴታው ፣ ነው ፣ (ቊጥር ፣ ፮፻፶፬ ።) ለቤተሰብ ፣ ጥቅም ፣ ሲባል ፣ አንዱ ፣ መሰል ፣ ሲጠይቅ ፣ የዚያኛውን ፣ አበር ፣ ደሞዞችና ፣ ከግል–ሀብት ፣ ንብረት ፣ ገቢን ፣ እንዲቀበልለት ፣ (አንዴም ፣ ለዚሁ ፣ ደረሰኝ ፣ እንዲሰጥለት ፣) የቤተ–ዘመዱ ፣ ገላጋዮች ፣ ለሌላው ፣ መሰይ ፣ ሊፈቅዱ ፣ ይችላሉ ፤ እንዲሁም ፣ ደግሞ ፣ ጥቅሞቹን ፣ ደሞዙንና ፣ ገቢውን ፣ በምሉ ፣ ወይም ፣ በከፊል ፣ በሰው ፣ ሰው ፣ እጅ ፣ እንዲያዙ ፣ (እንዲከበሩለት ፣) ለመፍቀድ ፣ ይችላሉ ። ይኸም ፣ ለምሳሌ ፣ ባለደሞዙን ፣ እንደተቀበለ ፣ ወዲያውኑ ፣ ገንዘቡን ፣ በመጠጥ ፣ ላይ ፣ ቢከሰክስ ፣ ደሞዙን ፣ በሚከፍለው ፣ ሰው ፣ በሰጡ ፣ እጆች ፣ እንዲያዝ ፣ (እንዲከበር ፣) ያዝዙ ፣ ዘንድ ፣ ሚስቲቱ ፣ የቤተ–ዘመድ ፣ ገላጋዮቹን ፣ ልትጠይቅ ፣ ትችላለች ፣ (ቊጥር ፣ ፮፻፶፭ ።)

ምንም ፣ እንኳ ፣ የጋራ ፣ ሀብት ፣ ንብረትን ፣ ባልየው ፣ ቢያስተዳድር ፣ ቅሉ ፣ እንዲህ ፣ ያለው ፣ ያስተዳደር ፣ ተግባሩ ፣ እንዳሻው ፣ ከጅ ፣ ለማስወጣትና ፣ ለማስተላለፍ፣ ለመሸጥ ፣ ለመለወጥ ፣ የሚያስችለው ፣ ባለ ፣ መብትነት ፣ አይደለም ፣ (የጋራ ፣ ሀብትን ፣ ሚስቲቱ ፣ እንድታስተዳድር ፣ አደራው ፣ በተጣለባት ፣ ጊዜም ፣ እንደዚሁ ፣ ነው ፣ አይፈቀድላትም ።) የጋራ ፣ ሀብት–ንብረትን ፣ ነክ ፣ በሆኑ ፣ ጉዳዮች ፣ በሚነጋገሩበት ፣ ጊዜ ፣ የሁለቱ ፣ አበሮች ፣ መስማማትን ፣ የሚያስፈልግበት ፣ አንዳንድ ፣ ነገሮች ፣ አሉ ፤ እሊህም ፤

ሀ/ የማይንቀሳቀስ ፡ የጋራ–ንብረትን ፡ ስም ፡ ባለቤት–ነት ፡ ማዛወር ፤

ለ/ ዋጋው ፡ ከኢ.ት/ $ 500 በላይ ፡ የሆነውን ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ የጋራ ፡ ሀብትን ፡ ስም ፡ ለሌላው ፡ ማዛወርና ፡ በሁለቱ ፡ አበሮች ፡ ስም ፡ የተመዘገቡትን ፡ ( ሴኩሪቲስ ፡ ) መያዣ/ ማገቻ ፡ ሰነዶች ፡ (ያበዳሪነት ፡ ማስረጃ ፡ የጥቅም ፡ ዕጣ ፡ እሊህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ሁሉ ፡ ) ባለቤት–ነት ፡ ለማስተላለፍ ፤

ሐ/ ከኢ.ት/ $ 100 ለሚልቅ ፡ ብድር ፡ ውል ፡ መግባት ፤ እና ፡

መ/ በዋጋው ፡ ከኢ.ት/ $ 100 ለሚልቅ ፡ ቢጤ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ስጦታ ፡ ማበርከት ወይም ፡ ከኢ.ት /$ 100 በላይ ፡ ለሚበደር ፡ ሰው ፡ ዋስ ፡ ሆኖ ፡ መቆም ፡ ናቸው።

በዚህ ፡ በላይ ፡ የተመለከቱትን ፡ ሕግ ፡ ነክ ፡ ተግባሮች ፡ ለማከናወን ፡ ስለሚያስፈልገው ፡ የአበሮቹ ፡ መስማማት ፡ ልዩ ፡ ያፈጻጸም ፡ ሥርዓቶች ፡ እንዲኖረው ፡ ሕጉ ፡ አያስገድድም ፤ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ስምምነት ፡ በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ ጽሑፍ ፡ ላይ ፡ ሲገባና ፡ የቃል ፡ ( ይህም ፡ ያስኬዳል/ ይመስላል ፡ ) ሊሆን ፡ ይችላል ። እንዲሁም ፡ አንዱ ፡ አበር ፡ ከሌላው ፡ አበሩ ፡ ጋራ ፡ ሳይግባባ ፡ ከላይ ፡ ከተመለከቱት ፡ ሕግ ፡ ነክ ፡ ተግባሮች ፡ ማናቸውንም ፡ አንዱን ፡ ቢያደርግ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ቅጣትን ፡ እንደሚያስከትልበት ፡ ሕጉ ፡ ለይቶ ፡ በጉልሕ ፡ አያብራራም ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለቅጣቱ ፡ ፍርድ ፡ ነክ ፡ ድርጊቱ ፡ በመጠኑ ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ ውጤት ፡ አልባና ፡ ባዶ ፡ ተብሎ ፡ ይገመገም ፡ ዘንድ ፡ ሐሳብ ፡ ቀርቧል ፡ ይኸም ፡ ማለት ፡ በጉዳዩ ፡ ያልተስማማው ፡ አበር ፡ ወራሾች ፡ ውጤት ፡ አልባነቱን ፡ መዳኛ ፡ ምክንያታቸው ፡ አድርገው ፡ ለመከራከር ፡ ይችላሉ ፡ ነው ። ዋጋ ፡ አልባነቱ ፡ የፍርድ ፡ ነክ ፡ የሆነውን ፡ ድርጊት ፡ የፈጸመውን ፡ አበር ፡ ( ራሱን ፡ ) ሊያድነው ፡ አይችልም ፡ እና ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ አበር ፡ በግል ፡ ሀብቱ ፡ በኩል ፡ የዚያኛው ፡ የፍርድ ፡ ነኩን ፡ ተግባር ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ለመፈጸም ፡ የተነጋገረው ፡ ሰው ፡ ተጠያቂ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይቀራል ።

ከአበሮቹ ፡ ከአንዱ ፡ ላይ ፡ የሚጠየቁት ፡ እዳዎች ፡ ከዚያው ፡ አበር ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ንብረትና ፡ ከጋራ ፡ ሀብት–ንብረት ፡ ላይ ፡ ተቀንሶ ፡ ሊመለስ ፡ ይቻላል ፡ እንጂ ፡ ከሌላው ፡ (ባለ ፡ እዳ ፡ ካልሆነው ፡ ) የግል ፡ ሀብትና ፡ ንብረት ፡ አይደለም ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፶፰ ።) ይህ ፡ አንቀጽ ፡ እንዲያው ፡ በደፈናው ፡ በአንዱ ፡ አበር ፡ የሚከፈሉ ፡ እዳዎችን ፡ ያወሳና ፡ የየእዳዎቹን ፡ ዓይነት ፡ አይለይም ፤ ስለዚህ ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ከጋብቻው ፡ በፊት ፡ ለገባባቸው ፡ እዳዎችና ፡ ደግሞ ፡ ውርስ ፡ ሲቀበል ፡ ( አብሮ ፡ ) የወረሳቸውን ፡ እዳዎች ፡ ካንደኛው ፡ አበር ፡ የግል ፡ ሀብት–ንብረቱና ፡ የጋራ ፡ ሀብት–ንብረቱ ፡ ላይ ፡ ተቀናሽ ፡ የሚሆኑ ፡ መስለው ፡ ይታያሉ ።

ለትዳር ፡ ጣጣ ፡ ሲባል ፡ የተገቡባቸው ፡ እዳዎች ፡ (እሊህም ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፷ ፡ ላይ ፡ ተዘርዝረዋል ፡ ) የሁለቱም ፡ አበሮች ፡ ያንድ ፡ ላይና ፡ የያንዳንዳቸው ፡ ( በነጠላ ፡ ) እዳዎች ፡ ናቸውና ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ከሁለቱም ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ንብረቱና ፡ ደግሞ ፡ ከጋራ ፡ ሀብት–ንብረቱ ፡ ላይ ፡ ተነስቶ ፡ ሊወጡቸው ፡ ይቻላል ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፶፱ ።) አበሮቹ ፡ ከአቅማቸው ፡ ጋራ ፡ ተመጣጣኝ ፡ የሆነ ፡ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ ወጭ ፡ መዋጮ ፡ እንዲመድቡ ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፷፩ ።) ለትዳሩ ፡ ጣጣ ፡ ሲባል ፡ የሚገቡባቸው ፡ እዳዎች ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ መሆናቸው ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፷ ፡ ተመልክተዋል ፡ እሊሁም ፤

ሀ/ ለቤተ ፡ ሰቡ ፡ መኖሪያ ፡ ( የኑሮ ፡ ጣጣ ፡ ) ምግብ ፡ ማደሪያ ፡ ልብስና ፡ የልጆች ፡ ትምህርት ፡ መማሪያ ፤

ለ/ ባንዱ ፡ አበር ፡ ወይም ፡ በሁለቱም ፡ አበሮች ፡ የሚከፈል ፡ ኑሮን ፡ ለመጠበቅ ፡ ምግብ ፡ ለመስጠት ፡ ያለን ፡ ግዴታ ፡ ለመምላት ፡ የገቡባቸው ፡ እዳዎች፤እና

ሐ/ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ እንደሊህ ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ የሚወስኗቸው ፡ ሌሎች ፡ እዳዎች፤የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ገላጋዮቹ ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ አበዳሪው ፡ ሲጠይቅ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ይችላሉ ።

## <u>፫ ፤ የጋብቻ ፡ መፍረስ ፡</u>

<u>የመፍረሱ ፡ መነሻ ፡ ምክንያቶች ፡</u>

የጋብቻ ፡ ወራት ፡ ዘመን ፡ የሚደመደምበት ፡ በሦስት ፡ መንገዶች ፡ ነው ፤

ሀ/ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ በሞት ፡ ሲለይ ፤

ለ/ ከጋብቻው ፡ አውራ ፡ ግዴታዎች ፡ አንዱ ፡ በመጣሱ ፡ ምክንያት ፡ በምጥንታ ፡ (ቅጣት) ድንጋጌዎች ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጋብቻው ፡ እንዲፈርስ ፡ ሲያዝ ፤ እና ፡

ሐ/ በፍቺ ፡ ነው ።

ሕጉ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ጋብቻዎች ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ አያደርግም፤ ጋብቻዎች ፡ ሁሉ ፡ የሃይማኖት ፡ ሆነ ፡ የብሔራዊ ፡ ወይም ፡ የልማድ ፡ የጋብቻ ፡ ወራት ፡ ከተባሉት ፡ ሦስት ፡ መንገዶች ፡ ውስጥ ፡ ባንዱ ፡ ከፍጻሜ ፡ ዘመኑ ፡ ይደርሳል ።

ጋብቻ ፡ በፍቺ  የሚደመደምባቸው ፡ ጠባይና ፡ ሁኔታዎች ፡ ለሁሉ ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነቶች ፡ አብነት ፡ ይሆናሉ ። ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ቍጥር ፡ ፮፻፷፬ ፡ እንደመደበው ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ በቃኸኝ ፡ (ወይም ፡ በቃሸኝ) አልፈልግም ፡ የማለት ፡ አለመፈለግን ፡ ፍቺ ፡ አይቆጥረውም፤ደግሞ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ በመስማማት ፡ በአበሮቹ ፡ የጋራ ፡ ፈቃድ ፡ የሚደረገው ፡ ፍቺ ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፷፮ ፡ የተከለከለ ፡ ነው ። ፍቺ ፡ ሊፈቀድ ፡ የሚቻለው ፡ በሕግ ፡ በተመሠረቱት ፡ ምክንያቶች ፡ ነው ፤ እሊህም ፡ መነሻ ፡ ምክንያቶች ፡ (ሀ) ከባድ ፡ ምክንያቶች ፡ እና ፡ (ለ) ሌላ ፡ ምክንያቶች ፡ ተብለው ፡ በሁለት ፡ ክፍል ፡ ተመድበዋል ። ለፍቺ ፡ ጥያቄ ፡ የሚቀርበው ፡ ለቤተዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አይደለም ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፷፰)፤ ይኸም ፡ በቍጥር ፡ ፮፻፸፯ ፡ የተወሰኑት ፡ ሰዎች ፡ ማለት ፡ ነው ። የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ለቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ ለተሰጡት ፡ ሥልጣኖች ፡ በጐደለ ፡ መምልያ ፡ ዘርፍ ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ የሥልጣን ፡ ዘርፍ ፡ የሚሆነውም ፡ ፍቺ ፡ ተነግሮ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ እንዳልሆነ ፡ ሊወስን ፡ ችሎታ ፡ ያለው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነው ፡ በሚለው ፡ አስተያየት ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፸፱) ። ይህም ፡ ማለት ፡ ሕጉ ፡ በሚፈቅደው ፡ መሠረት ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ገላጋዮች ፡ ፍቺ ፡ መናገራቸውን ፡ (መለፈፋቸውን) ሊያረጋግጥ ፡ የሚችል ፡ የመጨረሻው ፡ ሥልጣን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ (ከዚህ ፡ ግርጌ ፡ በተሰጡት ፡ ሁኔታዎች ፡ ካልሆነ ፡ በቀር) ነገሩ ፡ በመዠመሪያ ፡ ለቤተዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ ቀርቦ ፡ የነበረ ፡ ካልሆነ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለፍቺ ፡ የቀረበን ፡ ማመልከቻ ፡ ጥያቄ ፡ ለማየት ፡ ችሎታ ፡ የለውም ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ለመፋታት ፡ ሲባል ፡ የቀረበውን ፡ ማመልከቻ ፡ በሥርዓት ፡ መልክ ፡ ሊቀበልና ፡

ሊያውቀው ፡ የሚችለው ፡ ገላጋዮቹ ፡ በሕግ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ (ቁጥር ፡ ፮፻፷፫ ፡ እና ፡ ፮፻፸፫) ወይም ፡ ለአእምሮ ፡ ግምት ፡ ያጠግባል ፡ ተብሎ ፡ በሚገመገም ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ (ቁጥር ፡ ፯፻፴፯) ውሳኔ ፡ ለማድረግ ፡ በቃታቸው ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ለመፋታት ፡ ሲባል ፡ ለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ገላጋዮቹ ፡ የሚቀርበው ፡ ልመና ፡ (ጥያቄ) የሚደረገው ፡ ከአበሮቹ ፡ በንዱ ፡ ወይም ፡ በአበሮቹ ፡ በሁለቱም ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ እንጂ ፡ በማንም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሊሆን ፡ አይችልም ፤ እንዲሁም ፡ ከውሳኔ ፡ ከመደረሱ ፡ በፊት ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ የሞተ ፡ እንደሆነ ፡ የፍቺው ፡ ነገር ፡ እርምጃ ፡ ከፍጻሚ ፡ ከመድረሱም ፡ በላይ ፡ በሟቹ ፡ አበር ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ባለጥቅም ፡ ነን ፡ በዮች ፡ ሰዎች፡ ነገሩ ፡ እንዲቀጥል ፡ ለመቀስቀስ ፡ አይቻልም ፡ (ቁጥር ፡ ፮፻፷፯) ። ፍቺን ፡ ለመፍቀድ ፡ የሚያስችሉት ፡ ሁኔታዎችና ፡ ፍቺው ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ የተንጠለጠሉት ፡ ፍቺውን ፡ የለመነው ፡ አባሪ ፡ ጓደኛው ፡ ያጠፋው ፡ ጥፋት ፡ ለማፋታት ፡ ከባድ ፡ መነ ሾ ፡ ምክንያት ፡ ለመሆኑ ፡ ለማስረዳት ፡ በመቻሉ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ (ቁጥር፡፮፻፷፯)፤ ቁጥር፡ ፮፻፺—፮፻፺፫ ፡ በሌላ ፡ ከባድ ፡ ባልሆኑ ፡ ምክንያቶች ፡ እንዲፋታ ፡ በተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ የገንዘብ ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ፍቺው ፡ ስለሚያስከትለው ፡ ውጤቶች ፡ ያትታል ። የፍቺው ፡ ልመና ፡ ያለጥርጥር ፡ በታወቁ ፡ ከባድ ፡ ምክንያቶች ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ሲሆን ፡ የቤተሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ ልመናው ፡ ከቀረበላቸው ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ውሳኔአቸውን ፡ መስጠት ፡ አለባቸው ፤ (ማሳሰቢያ፤ ቁጥር ፡ ፮፻፷፰ ፡ በእንግሊዝኛው ፡ ትርጉም ፡ የውሳኔውን ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ወራት ፡ ይለዋል ። በፈረንሣይኛው ፡ የሕጉ ፡ ዋና ፡ ቅጂ ፡ ጽሑፍ ፡ ይኸው ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ወራት ፡ ተብሎ ፡ ተገልጿል ) ።

የፍቺ ፡ መነሾ ፡ ከባድ ፡ ምክንያቶች ፡ ሁለት ፡ አይነቶች ፤

ሀ/ አጥፊነቱ ፡ በአበሩ ፡ ላይ ፡ የሚጣል ፡ ሲሆን ፡ እና ፡

ለ/ ከአበሩ ፡ የፈቃድ ፡ ኃይል ፡ (አቅም) የተለዩት ፡ ምክንያቶች ፡ ናቸው ። ለመ ዠመሪያው ፡ ክፍል ፡ የተመደቡት ፤

(፩) ዝሙት ፡

(፪) ለሁለት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ አድራሻው ፡ በማይታወቅበት ፡ መልክ ፡ አበሩ ፡ ከጋ ብቻ ፡ ሰፈሩ ፡ ከቤቱ ፡ ኮብልሎ ፡ ሲጠፋ ፡ ነው ፡ (ቁጥር ፡ ፮፻፷፱) ።

ለሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ የተመደቡት ፤

(፩) እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ለሁለት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ አእምሮው ፡ ተናውጾበት ፡ በእ ብዶች ፡ ሠፈር ፡ (መምሕፃን ፡ ሲዘጋበት፤)

(፪) በአድራሻው ፡ መታጣቱ ፡ በፍርድ ፡ ሲረጋገጥ ፡ (ቁጥር ፡ ፮፻፸፪ ፤)እና ፡

(፫) የሃይማኖት ፡ ጋብቻን ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣን ፡ መሻሩን ፡ ሲያስታውቅ (ቁጥር ፡ ፮፻፸፩ ።) ናቸው ።

በሃይማኖት ፡ ሥርዓት ፡ የተከናወነን ፡ ጋብቻ ፡ የሃይማኖት ፡ ባለሥልጣን ፡ መሻር ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፤ የፍቺ ፡ መነሻ ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑ ፡ የሚቀረው ፡ አበሮቹ ፡ ጋብቻው ፡ እንደተሻረ ፡ እያወቁ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ መኖራቸውን ፡ ሲቀጥሉ ፡ ነው፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከባድ ፡ እንዳይደለ ፡ የፍቺ ፡ ምክንያት ፡ ሊቆጠር ፡ ይችላል ።

ኃላፊነቱ ፣ በአበሩ ፣ ላይ ፣ ስለሚወድቁበት ፣ የፍቺ ፣ ከባድ ፣ ምክንያቶችን ፣ ለሚ መለከተው ፣ ጉዳይ ፤ እነዚህ ፣ የፍቺ ፣ ከባድ ፣ ምክንያቶች ፣ ከመሆናቸው ፣ የሚገላግል ፣ ያላጠፋው ፣ አበር ፣ ኃጥኡን ፣ በጠፋው ፣ ጥፋት ፣ ይቅር ፣ ብሎ ፣ ሲያልፈው ፣ ነው ፤ የኃ ጢአተኛው ፣ ምግባር ፣ ከቋረጠ ፣ በኋላ ፣ እስኪ ፣ ስድስት ፣ ወር ፣ ድረስ ፣ ለመፋታት ፣ አ ቤቱታ ፣ ካልቀረበም ፣ ያው ፣ ይቅርታ ፣ መደምደሚያ ፣ ይሆናል ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፸፱ ።)

ከባድ ፣ ባልሆኑ ፣ ምክንያቶች ፣ የተነሣ ፣ ለመፋታት ፣ በሚቀርብ ፣ ጥያቄ ፣ በአበሮቹ ፣ መከከል ፣ እርቅና ፣ስምምነት ፣ እንዲወርድ ፣ መጣሩ ፣ የቤተ ፣ ሰቡ ፣ ገላጋዮች ፣ ግዴታ ፣ ነው ፣ ከዚሁ ፣ ዓላማቸው ፣ ለመድረስ ፣ ሲሉም ፣ ለማስታረቅና ፣ ለማስማማት ፣ ይበጃል ፣ የሚሉዋቸውን ፣ አስተያየቶችን ፣ ሁሉ ፣ ሊወስኑ ፣ ይችላሉ ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፸፮ ።) ለማስ ታረቅ ፣ ያቃታቸው ፣ እንደሆነም ፣ በፍቺው ፣ ቅጥና ፣ ሁኔታዎችን ፣ (ማለት ፣ ፍቺው ፣ በገንዘባቸው ፣ ላይ ፣ ስለሚያስከትለው ፣ ውጤቶች ፣ ስለ ፣ ኑሮ ፣ አጠባበቅ ፣ መተዳደሪያ ፣ እና ፣ ስለ ፣ ሕፃናት ፣ ሞግዚትነት ፣ መብት ፣ ነክ ፣ በሆኑት ፣ ጉዳዮች ፣ ላይ ፣ ) አበሮቹ ፣ እንዲስማሙ ፣ የቤተ ፣ ሰቡ ፣ ገላጋዮች ፣ አበሮቹን ፣ ለማግባበት ፣ እንዲጥሩ ፣ ያስፈል ጋል ። አበሮቹም ፣ ከንዲህ ፣ ያሉው ፣ ስምምነት ፣ ላይ ፣ ሲደርሱ ፣ አበሮቹ ፣ ከተስማሙ በት ፣ ግዴታዎችና ፣ አኳኋን ፣ ጋራ ፣ በሚግባቡ ፣ መልክ ፣ የቤተ ፣ ሰቡ ፣ ገላጋዮች ፣ ይበ ይናሉ ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፸፯) ፤ ምን ፣ ጊዜም ፣ ቢሆን ፣ ብይኑ ፣ የሚጸድቀው ፣ በቍጥር ፣ ፮፻ ፸፱ ፣ መሠረት ፣ ፍቺው ፣ መነገሩን ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ ሲያረጋግጥ ፣ ነው ። አበሮቹ ፣ በይታ ረቁ ፣ ወይም ፣ ስለ ፣ ፍቺው ፣ ግዴታዎች ፣ ከስምምነት ፣ ላይ ፣ ሳይደርሱ ፣ ቢቀሩ ፣ ለመ ፋታት ፣ ጥያቄው ፣ ከደረሰበት ፣ ዕለት ፣ ጕምሮ ፣ ባለው ፣ አንድ ፣ ዓመት ፣ ውስጥ ፣ የቤተ ፣ ዘመዱ ፣ የሽምግልና ፣ ዳኞች ፣ የፍቺ ፣ ውሳኔ ፣ ያደርጋሉ ። ሆኖም ፣ ይህ ፣ የአንድ ፣ ዓመ ት ፣ ጊዜ ፣ በአበሮቹ ፣ ስምምነት ፣ ወደ ፣ አምስት ፣ ዓመት ፣ ዕድሜ ፣ ሊራዘም ፣ ይችላል ። ስለዚሁ ፣ ጉዳይ ፣ አበሮቹ ፣ ከመጋባታቸው ፣ በፊት ፣ ወይም ፣ በኋላ ፣ በዚሁ ፣ መልክ ፣ ሊስማሙበት ፣ ይችላሉ ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፸፰ )።

ከባድ ፣ ከሆኑ ፣ ወይም ፣ ከባድ ፣ ካልሆኑ ፣ ምክንያቶች ፣ የተነሣ ፣ ለቤተ—ሰቡ ፣ የሽ ምግልና ፣ ዳኞች ፣ የፍቺ ፣ ጥያቄ ፣ በቀረበ ፣ ጊዜ ፣ ቁርጥ ፣ ውሳኔአቸውን ፣ እስከሚሰጡ ፣ ድረስ ፣ የቤተ—ዘመድ ፣ ገላጋዮች ፣ አበሮቹንና ፣ ልጆቹን ፣ (ሕፃናቱን ፣) ለመደገፍ ፣ አስ ፈላጊ ፣ ሊሆኑ ፣ ስለሚችሉት ፣ ነገሮች ፣ ቋሚ ፣ ያልሆኑ ፣ የጊዜው ፣ ትእዛዞችን ፣ ሊሰጡ ፣ ይችላሉ ። ይኸም ፣ ማለት ፣ ስለ ፣ አበሮቹና ፣ ስለልጆቹ ፣ መተዳደሪያ ፣ አበል ፣ ስለ ፣ አበ ሮቹ ፣ ሀብት ፣ ንብረት ፣ አስተዳደር ፣ ስለ ፣ አበሮቹ ፣ መኖሪያ ፣ ሥፍራ ፣ የጊዜው ፣ የሆኑ ፣ ትእዛዞችን ፣ ሊወስኑ ፣ ይችላሉ ፣ ነው ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፹፬ )። እሊህን ፣ ማናቸውንም ፣ የጊ ዜው ፣ ትእዛዞች ፣ ሊያስረዱት ፣ ለሚቻል ፣ በጎ ፣ ተግባር ፣ ሲባል ፣ በማናቸውም ፣ ምክ ንያት ፣ እንደገና ፣ ከልሶ ፣ ለመለዋወጥ ፣ ወይም ፣ ለመሰረዝ ፣ ይቻላል ፣ (ቍጥር ፣ ፮፻፹፭)።

የቤተ—ሰቡ ፣ ገላጋዮች ፣ የመጨረሻውን ፣ ውሳኔአቸውን በሚያደርጉበት ፣ ጊዜ ፣ ፍቺውን ፣ የሚናገር/ የሚያጕላ ፣ ብይንን ፣ ይሰጣሉ ። ደግሞም ፣ በእንደዚህ ፣ ያለው ፣ ብይን ፣ ውስጥ ፣ ከቍጥር ፣ ፮፻፺ — ፮፻፺፭ ፣ ድረስ ፣ ከተመለከቱት ፣ ደንቦች ፣ ጋራ ፣ በሚ ዋደድ ፣ መልክ ፣ ከጋብቻው ፣ የተወለዱት ፣ ሕፃናት ፣ በማንኛው ፣ እጅ ፣ እንደሚጠበቁ ፣ (በማን ፣ ሞግዚትነት ፣ እንደሚኖሩ ፣ ) እና ፣ ስለ ፣ አበሮቹ ፣ የግልና ፣ የጋራ ፣ ሀብትና ፣ ንብረት ፣ ሂሳብ ፣ ማጣራት ፣ ስለሚመለከቱት ፣ ጉዳዮች ፣ ትእዛዞችን ፣ እንዲሰጡ ፣ ያስ ፈልጋል ። ከፍቺው ፣ መግለጫ ፣ ውስጥ ፣ በመጀመሪያው ፣ ብይን ፣ ያልተብራራ ፣ አከራ ካሪ ፣ ነገር ፣ ቢነሣ ፣ የቤተ-ዘመድ ፣ የሽምግልና ፣ ዳኞቹ ፣ እሊሁኑ ፣ ከፍቺው ፣ በኋላ ፣ የተቀሰቀሱትን ፣ ጉዳዮች ፣ ( የሚያስተኛ ፣ ) የሚያስተካክል ፣ ተጨማሪ ፣ ብይንን ፣ ሊሰ

ጡ ፡ ይችላሉ ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ በጎደል ፡ መላ ፡ ዘርፍ ፡ ( ተጨማሪ ፡ ) ብይን ፡ የመዠመሪያው ፡ ብይን ፡ ከተሰጠበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ከስድስት ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ ሊሰጥ ፡ አይቻልም ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፹) ። ስለ ፡ ልጆቹ ፡ (አቃቢነት ፡ ) መጠበቅ ፡ (ማለት ፡ ከአባትየው ፡ ዘንድ ፡ ወይስ ፡ ከናቲቱ ፡ ዘንድ ፡ ሁነው ፡ ይጠበቁ ፡ ብሎ ፡ ስለመወሰኑ) እና ፡ ስለ ፡ አያያዛቸው ፡ አስተዳደር ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ ማናቸውን ፡ ትእዛዞች ፡ በሚሰጡበት ፡ ላይ ፡ አውራ ፡ ጉዳይ ፡ ሆኖ ፡ ሊታይ ፡ የሚገባው ፡ የሕፃናቱ ፡ ጥቅም ፡ ነው ። የቤተ ፡ ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ በምድራዊው ፡ እና ፡ በትክክለኛው ፡ በጎ ፡ ምግባር ፡ ( ሞራል )፡ በሁለቱም ፡ በኩል ፡ የልጆቹን ፡ ምቾት ፡ ብቻ ፡ በመመልከት ፡ እንዲወስኑ ፡ ያስፈልጋል። ሕፃናት ፡ በናቲቱ ፡ ባለ ፡ አደራነት ፡ እንዳይቀመጡ ፡ የሚከላ ፡ ከባድ ፡ ምክንያት ፡ ከሌለ ፡ የአምስት ፡ ዓመትና ፡ በዕድሜያቸው ፡ ከዚያ ፡ በታች ፡ የሆኑት ፡ የለጋ ፡ (ጨርቋ ፡) ዕድሜ ሕፃናት ፡ አደራ ፡ ጠባቂነት ፡ በናቲቱ ፡ ላይ ፡ እንዲጣል ፡ ያስፈልጋል። ልጆችን ፡ ስለሚመከት ፡ በማናቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ለልጆቹ ፡ መልካም ፡ እድገት ፡ ጥቅም ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ በማናቸውም ፡ ሰዓት ፡ እንደገና ፡ ተመርምሮ ፡ ሊለዋወጥና ፡ ሊስተካከል ፡ ይገባል ። ይኸም ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ በናቲቱ ፡ ባለአደራ ፡ ጠባቂነት ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ እናቲቱ ፡ ከበጎውና ፡ ከትክክለኛው ፡ ቀን ፡ ምግባር ፡ ውጭ ፡ የሆነ ፡ አኑዋኗር ፡ ብትይዝ ፡ ትእዛዙ ፡ እንደገና ፡ ታይቶ ፡ አባትየው ፡ የልጆችን ፡ አቃቢነት ፡ ተግባር ፡ በሚገባ ፡ ለማከናወን ፡ የበቃ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ የጠባቂነት ፡ ባለአደራ ፡ ሞግዚትነቱ ፡ ለርሱ ፡ ይሰጣል ። ልጆችን ፡ ነክ ፡ ስለሆነው ፡ ትእዛዝ ፡ እንደገና ፡ ታይቶ ፡ እንዲለወጥ ፡ ጥያቄን ፡ ለቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ የሚያቀርብ ፡ የልጆቹ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ወይም ፡ ማንኛውም ፡ አውራጅ ፡ ዘመድ ፡ ነው ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፹፩ ፡ እና ፡ ፮፻፹፪።)

## ጋብቻ ፡ ሲፈርስ ፡ በአበሮቹ ፡ መካከል ፡ ያለን ፡ የገንዘብ ፡ ሀብት ፡ ግንኙነት ፡ ማጣራት ።

በአበሮቹ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የገንዘብ ፡ ሀብት ፡ ግንኙነት ፡ የማጣራቱ ፡ ተግባር ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ መንገዶች ፡ በማናቸውም ፡ አንድ ፡ የመፍረሻ ፡ መንገድ ፡ ጋብቻ ፡ ሲፈርስ ፡ የሚያስከትለው ፡ አውራ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ እንደጋብቻው ፡ አፈራረስ ፡ መንገድ ፡ (ማለት ፡ በሞት ፡ በፍቺ ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ግዴታዎች ፡ አንዱ ፡ በመጣሱ ፡ በምጥንታ ፡ ድንጋጌ ፡ እንደ ፡ መፍረስ) ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ አለው ። በክርክር ፡ ላይ ፡ የተንጠለጠለው ፡ የጋብቻ ፡ ዓይነት ፡ ብሔራዊ ፡ ወይም ፡ የሃይማኖት ፡ ወይም ፡ የልማድ ፡ ቢሆን ፡ የሀብት ፡ ግንኙነትን ፡ የማጣራት ፡ ተግባርን ፡ የሚዳኙት ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦች ፡ ከጋብቻው ፡ መንገዶች ፡ የተለዩ ፡ ራሳቸውን ፡ የቻሉ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የማይለዋወጡ ፡ ለሁሉም ፡ ዓይነት ፡ ጋብቻዎች ፡ ያው ፡ የሆኑ ፡ ናቸው ።

ሀ/ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ በሞት ፡ በመለየቱ ፡ ምክንያት ፡ ጋብቻው ፡ ስለፈረሰ ፡ የሚያመጣው ፡ የማጣራት ፡ ተግባር ፡

አበሮቹ ፡ የግልና ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረቱን ፡ አከፋፈል ፡ መልክና ፡ ቅጥ ፡ የሚዳኝ ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ገብተው ፡ እንደሆነ ፡ የሀብት ፡ ግንኙነት ፡ ማጣራቱ ፡ ተግባር ፡ ከውሉ ፡ ጋራ ፡ በሚዋደድ ፡ መልክ ፡ ይከናወናል ። በባልና ፡ ሚስቱ ፡ መካከል ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ውል ፡ ከሌለ ፡ ግን ፡ የማጣራቱ ፡ ተግባር ፡ በሕግ ፡ ከተወሰኑት ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦች ፡ ጋራ ፡ በሚስማማ ፡ መልክ ፡ ይፈጸማል ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፺፫) ።

የመዠመሪያው ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ እያንዳንድ ፡ አበር ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ንብረቱ ፡ ሁኖ ፡ የተመደበውን ፡ ይዞ ፡ እንዲሄድ ፡ የሚያስችል ፡ ነው ፡ (ቍጥር ፡ ፳፻፹፬) ። ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ የግል ፡ ሀብቱ ፡ ባለቤትነት ፡ መብቱ ፡ እጅ ፡ ስም ፡ ተዛውሮበትና ፡ መዘዋወሩ ፡ ያስገኘውም ፡ ሀብት ፡ ከጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረቱ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ መቀላቀሉን ፡ ሊያስረዳ ፡ ከቻለ ፤ እንኪያስ ፡ ይኸው ፡ አበር ፡ የግል ፡ ሀብቱ ፡ ባለቤትነት ፡ እጅ ፡ ሲዛወር ፡ ያስገኘው ፡ ዋጋ ፡ ልክን ፡ የሚያህል ፡ በገንዘብ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ነገሮች ፡ መልክ ፡ ከጋራው ፡ ሀብት ፡ ቀንሶ ፡ ሊወስድ ፡ መብት ፡ አለው ። ሁለቱም ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ በዚህ ፡ መልክ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ዕቃዎች ፡ ቀንሶ ፡ የመውሰድ ፡ መብት ፡ ያሏቸው ፡ እንደ ሆነ ፡ እንግዲያስ ፡ ሚስቲቱ ፡ (ወይም ፡ ወራሾቿ ፡ እንደአጋጣሚውና ፡ እንደ ሁኔታው) ድርሻዋን ፡ በቀዳሚነት ፡ ቀንሳ ፡ ለመውሰድ ፡ ዕድል ፡ አላት ፡ ቍጥር ፡ ፳፻፹፭ )። ይህም ፡ የቀዳሚነት ፡ ዕድል ፡ ለሚስቲቱ ፡ የተሰጣት ፡ እንደደንቡ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረትን ፡ የሚያስተዳድረው ፡ አበር ፡ ባልየው ፡ ስለ ሆነ ፡ ነው ።

አንዱ ፡ አበር ፡ በሠራው ፡ ድርጊት ፡ ምክንያት ፡ የሌላው ፡ አበር ፡ የግል ፡ ሀብትን ፡ ወይም ፡ የጋራ ፡ ሀብታቸውን ፡ በጎዳ ፡ ጊዜ ፡ ተበዳዩ ፡ አበር ፡ ካሣ ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ ለመቀበል ፡ መብት ፡ የሚኖረው ፤

ሀ/ ድርጊቱን ፡ የፈጸመው ፡ አበር ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ድርጊት ፡ ለመፈጸም ፡ ምንም ፡ መብት ፡ ሳይኖረው ፡ የቀረ ፡ እንደሆነ ፤ ወይም ፡

ለ/ የተፈጸመው ፡ ድርጊት ፡ የብልሹ ፡ መጥፎ ፡ አስተዳዳሪነት ፡ ፍሬ ፡ ወይም ፡ የሌላውን ፡ አበር ፡ መብቶች ፡ በማጭበርበርና ፡ በማታለል ፡ የተፈጸመ ፡ ድርጊት ፡ ሲሆን ፡ ነው ።

ለ "ሀ" የሚሆነው ፡ ምሳሌ ፡ በቍጥር ፡ ፳፻፺፰ ፡ የተመለከቱትን ፡ የሁለቱም ፡ አበሮች ፡ ስምምነት ፡ በሚያስፈልግባቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ፍርድ ፡ ነክ ፡ ድርጊቶች ፡ ያለሚስቲቱ ፡ ስምምነት ፡ ባልየው ፡ ፈጽሞት ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ለእንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ድርጊቶች ፡ ኪሣራዎችን ፡ የሚወስነው ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ አዛዥ ፡ ድንጋጌ ፡ ስለሆነ ፡ ከእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ግዴታ ፡ ለማምለጥ ፡ አበሮቹ ፡ ስምምነት ፡ ለመግባት ፡ አይችሉም ። ደግሞም ፡ የማጣራቱ ፡ ተግባር ፡ ቢከናወንና ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ለመከናወኑ ፡ ደረሰኝ ፤ ቢሰጥም ፡ ቃሉ ፡ ድንጋጌው ፡ ቆራጭ ፡ አዛዥ ፡ ድንጋጌ ፡ ስለሆነ ፡ ምንጊዜም ፡ ውጤት ፡ አለው ፡ (ቍጥር ፡ ፳፻፹፮) ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ካሣ ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ ለመጠየቅ ፡ የሚቻልበት ፡ አበሩ ፡ በሞት ፡ ከተለየበት ፡ ዕለት ፡ ዠምሮ ፡ ወደኋላ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ ከማይልቅ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ የተፈጸሙ ፡ ድርጊቶችን ፡ በሚመለከቱ ፡ ጉዳዮች ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ (ቍጥር ፡ ፳፻፹፯) ። እንዲሁም ፡ የሌላው ፡ አበር ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ንብረት ፡ የዚህኛውን ፡ አበር ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ንብረትን ፡ ወይም ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረቱን ፡ ረግጦ ፡ በመጉዳት ፡ የጸጋው ፡ (የሀብቱ ፡ ) ዋጋ ፡ መጠን ፡ መትረፍረፉን ፡ (መዳበሩን) ሊያስረዳ ፡ የሚችለው ፡ አበር ፡ ካሣ ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አለው ፡ (ቍጥር ፡ ፳፻፹፰) ። እንዲሁም ፡ ባል ፡ በተለየ የግሉ ፡ ቤት ፡ የሆነውን ፡ ለመጠገን ፡ (ለማሻሻል) የሚስቲቱ ፡ የተለየ ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ ከሆነው ፡ ቢበደርና ፡ እዳውን ፡ መልሶ ፡ ለመክፈል ፡ ከመቻሉ ፡ በፊት ፡ ቢሞት ፡ ሚስቲቱ ፡ ኪሣራ ፡ ለመቀበል ፡ ባለ መብት ፡ ነች ።

የጋራ ፡ ሀብቱን ፡ የሚመለከቱ ፡ ዕዳዎች ፡ (ለምሳሌ ፡ ለትዳር ፡ ጥቅም ፡ ሲባል ፡ የገቡባቸው ፡ ዕዳዎች) ሁሉ ፡ ከተቀነሱበት ፡ በኋላ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረቱ ፡ ከሞት ፡ በተረፈው ፡ አበርና ፡ በሚቹ ፡ አበር ፡ ወራሾች ፡ መካከል ፡ እኩል ፡ ይተነተናል ። አበሮቹ ፡ በጋብቻ ፡ ውሉ ፡ ወይም ፡ በማናቸው ፡ ሌላ ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ ሀብት ፡ ንብረት ፡ እኩል ፡ በእኩል ፡ ሳይሆን ፡ (በተለያዩ) ክፍና ፡ ዝቅ ፡ በሚሉ ፡ ድርሻዎች ፡ ይከፈል ፡ ዘንድ ፡ ሊስማሙ ፡ ይችላሉ ፡ (ቁጥር ፡ ፮፻፹፱) ። ከዚህ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ነክ ፡ ከሆነው ፡ የሚነሳው ፡ አሻሚውና ፡ አከራካሪው ፡ ጉዳይ ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ሲሞት ፡ ውጤት ፡ የሚያገኘው ፡ ማናቸውም ፡ የስምምነት ፡ ግዴታ ፡ የሕጉ ፡ ቁጥር ፡ ፩ሺ፩፻፲፬ ፡ ተቃራኒ ፡ ነውን ፡ ወይንስ ፡ አይደለም ፡ የሚለው ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ ይዞት ፡ ላይ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ አንድም ፡ የተሰጠ ፡ የፍርድ ፡ ውሳኔ ፡ የለም ።

ለ/ ጋብቻ ፡ በፍቺ ፡ ሲፈርስ ፡ ስለማጣራት ፡ ተግባር ፤

ለመፋታት ፡ በተፈቀደ ፡ ጊዜ ፡ የግልና ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረት ፡ በንዴት ፡ ያለ ፡ አኳኋን ፡ እንዲጣራ ፡ የመወሰኑ ፡ ጉዳይ ፡ የቤተሰቡ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ውሳኔአቸውን ፡ እንዲሰጡባቸው ፡ ከተመደቡት ፡ ጉዳዮች ፡ አንዱ ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያለን ፡ ውሳኔ ፡ በሚያደርጉበትም ፡ ጊዜ ፡ የቤተዘመድ ፡ ገላጋይ ፡ ዳኞቹ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ከቁጥር ፡ ፮፻፺ ፡ እስከ ፡ ቁጥር ፡ ፮፻፺፮ ፡ የተጣሉትን ፡ መሠረተ ፡ ሐሳቦች ፡ መከተል ፡ ይገባቸዋል ። በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ ሲመለከቱት ፡ የማጣራቱ ፡ ተግባር ፡ እንደዚያው ፡ ጋብቻ ፡ በሞት ፡ መለያየት ፡ ሲፈርስ ፡ እንደሚደረገው ፡ ያለ ፡ ነው ፡ (ቁጥር ፡ ፮፻፺) ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ መሠረተ ፡ ሐሳብ ፡ በላይ ፡ በተጨማሪ ፡ ሕጉ ፡ ከፍቺው ፡ በፊት ፡ በአበሮቹ ፡ መካከል ፡ የተፈጸመ ፡ የጋብቻ ፡ ውል ፡ ወይም ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ስምምነት ፡ ሊለዋውጣቸው ፡ የማይቻለውን ፡ አንዳንድ ፡ ደንቦችን ፡ ይወስናል ፡ (ቁጥር ፡ ፮፻፺ (፪)) ።

በጋብቻው ፡ በዓል ፡ አሳቦ ፡ ወይም ፡ ጋብቻው ፡ በማለቱ ፡ ምክንያት ፡ የተሰጣጡትን ፡ ስጦታዎች ፡ ሁሉ ፡ የቤተሰቡ ፡ ገላጋዮቹ ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ሊያዝዙ ፡ ይችላሉ ። ስጦታውን ፡ ያበረከተው ፡ ሰው ፡ ከአበሮቹ ፡ አንዱ ፡ ለሌላው ፡ አበር ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ለአበሮቹ ፡ ያደረጉት ፡ ቢሆን ፡ አበርካቹ ፡ እንዲመለስለት ፡ ከጠየቀ ፡ ይመለስለታል ፤ እንዲሁም ፡ ስጦታውን ፡ ያበረከተው ፡ ሞቶ ፡ እንደሆነም ፡ ወራሾቹ ፡ እንዲመለስላቸው ፡ ሊጠይቁ ፡ ይችላሉ ። በጋብቻው ፡ ሥነ ፡ በዓል ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ጋብቻውን ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ለአበሮቹ ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ አንዱ ፡ ከሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ ሊገባበት ፡ ይችል ፡ የነበረውን ፡ ወይም ፡ የገባውን ፡ የማናቸውንም ፡ የጥቅሞች ፡ ተስፋ ፡ ቃልን ፡ የቤተሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ ሊሠርዙት ፡ ይችላሉ ፡ (ቁጥር ፡ ፮፻፺፩) ። እነሆ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ ልክን ፡ ቆርጦ ፡ በየወሩ ፡ ከአበሮቹ ፡ ላንዱ ፡ ለመክፈል ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ቢገባ ፡ ወይም ፡ ለጋብቻ ፡ መገላገያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ሀላዊን ፡ ሳይለውጥ ፡ እንዲኖርበትና ፡ እንዲጠቀምበት ፡ አንድ ፡ ቤትን ፡ ከአበሮቹ ፡ ላንዱ ፡ ሰጥቶት ፡ እንደነበረ ፡ የቤተዘመድ ፡ ገላጋዮች ፡ ዳኞቹ ፡ ይህንኑ ፡ ለአበሩ ፡ ተሰጥቶ ፡ የነበረውንና ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ጥቅም ፡ ሊሠርዙበት ፡ ይችላሉ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ስለጋራውና ፡ ስለ ፡ የግል ፡ ሀብት ፡ ንብረቱ ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፡ በሚነጋገሩበት ፡ ጊዜ ፡ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ፍቺውን ፡ ያስከተ

ለው ፡ መነሾ ፡ ምክንያት ፡ ከባድ ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ ያይደለ ፡ እንደሆነ ፡ መመ ርመር ፡ አለባቸው ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የፈቺው ፡ መነሾ ፡ ምክንያትን ፡ ያመ ጣው ፡ ጥፋት ፡ ወደአንዱ ፡ አባሪ ፡ የጠባይ ፡ ጉድለት ፡ የሚያመራ ፡ እንደሆነ፡ መለየት ፡ አለባቸው ።

የፍቺው ፡ መነሾ ፡ ምክንያት ፡ ከባድ ፡ ሆኖ ፡ ጥፋቱ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ አባሪ ፡ ጠባይ፡ ጉድለት ፡ ሲያዘም ፤ አጥፊው ፡ አባሪ ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረቱን ፡ በምሉ ፡ ላላጠፋው ፡ አባሪ ፡ እንዲተውለት ፡ ሊታዘዝ ፡ ይቻላል ። እንደዚሁም ፡ አጥ ፊው ፡ አባሪ ፡ ከግል ፡ ሀብቱ ፡ ውስጥ ፡ ከሚሆ ፡ (ከአንድ ፡ ሦስተኛ ፡ )የማይል ቀውን ፡ ዕጣ ፡ ክፍሎ ፡ ላላጠፋው ፡ (ንጹሕ ፡ )አበሩ ፡ እንዲተውለት ፡ ሊታ ዘዝ ፡ ይቻላል ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ መቀጫም ፡ (ቅጣት ፡ ) በቍጥር ፡ ፮፻፷፮ ፡ እንደተመለከተው ፡ ስለስጦታዎች ፡ መልስ ፡ ለሰጭ ፡ ማስረከብ ፡ ከተወሰነው ፡ በላይ ፡ በተጨማሪ ፡ ሊጣል ፡ ይቻላል ። መቀጫዎቹም ፡ ጥፋት ፡ አልባ ፡ በሆ ነው ፡ አበር ፡ ላይ ፡ ከቶ ፡ ሊጣሉበት ፡ አይቻልም ። ወይም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የፍቺው ፡ መነሾ ፡ ምክንያት ፡ ከባድ ፡ ቢሆንም ፡ ቅሉ ፡ አጥፊነቱ ፡ በማያመራ በት ፡ አበር ፡ ላይ ፡ መቀጫዎቹ ፡ ሊጣሉበት ፡ አይቻልም ፡ በእንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ የሀብት ፡ ግንኙነትን ፡ የማጣራቱ ፡ ተግባርም ፡ እንደዚያው ፡ ጋብቻ ፡ በሞት ፡ በመለያየት ፡ ሲፈርስ ፡ እንደሚደረገው ፡ ያለ ፡ ነው ።

የፍቺው ፡ መነሾ ፡ ከባድ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ከላይ ፡ የተዘረ ዘሩት ፡ መቀጫዎች ፡ (ማለት ፡ ስጦታዎችን ፡ መመለስ ፡ — ቍጥር ፡ ፮፻፷፮ ፡ እና ፡ የጋራ ፡ ሀብት ፡ ንብረትንና ፡ ከግል ፡ ሀብቱ ፡ የተቆረጠ ፡ ድርሻ ፡ በመቀጫ ፡ መልክ ፡ መስጠቱ ፡ — ቍጥር ፡ ፮፻፷፯ ፡ ) ፍቺውን ፡ በጠየቀው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ይወድቅበት ፡ ዘንድ ፡ ማዘዝ ፡ ይቻላል ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፷፰)። ይህ ፡ ሕግ ፡ ያለመው ፡ ከከበዱት ፡ መነሾ ፡ ምክንያቶች ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ካልተመሠረተ ፡ በቀር ፡ የፍቺ ፡ ጥያቄዎች ፡ እንዳይቀርቡ ፡ ለማጣጣል ፡ (ላለመደፋፈር ፡ )ነው ፡ የፍቺው ፡ ምክንያት ፡ ከባድ ፡ ባልሆነበት ፡ ላይ ፡ እንዲፋታ ፡ ልመናውን ፡ የሚ ያሚቀርበው ፡ ሰው ፡ (ራሱ ፡ )የመፋታቱን ፡ ፈቃድ ፡ ማግኘቱ ፡ በገንዘብ ፡ ሀብት ፡ በኩል ፡ እንደሚያዋጣው ፡ (እንደማያተርፈው ፡ )ሊያውቀው ፡ ይች ላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ የቤተ ፡ ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ የተጠቀሱትን ፡ መቀጫዎች ፡ ከግብር ፡ ላይ ፡ ያውሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ቢገባ ፡ መቀጫዎቹን ፡ በምን ፡ መልክና ፡ ጠባይ ፡ ዘመሰላቸ ውና ፡ ይበጃል ፡ በሚሉበት ፡ መንገድ ፡ በግብር ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ ማደላደሉ ፡ የነርሱ ፡ ፈንታ ፡ ነው ። የቤተዘመድ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞች ፡ ስለመቀጫዎች ፡ (ቍጥር ፡ ፮፻፷፮ ፡ እና ፡ ፮፻፷፯ ፡ )የሰፈሩትን ፡ ደንቦች ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ ጨፍነው ፡ የሚከተሏቸው ፡ አይ ደሉም ፤ በግብር ፡ ላይ ፡ ሊያውሏቸውም ፡ ይችላሉ ፤ በኀሊናቸው ፡ እንደመሰላቸውና ፡ ይበጃል ፡ ብለው ፡ እንደሚገምቱት ፡ ደንቦቹን ፡ በምሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ በግብር ፡ ላይ ፡ ሊያውሏቸውም ፡ ይችላሉ ። ይህን ፡ በነጻ ፡ እንደመሰላቸው ፡ የመወሰን ፡ ተግባር ከፍና ዝቅ ፡ እያደረጉ ፡ በሚገለገሉበት ፡ ጊዜ ፡ ለድርጊታቸው ፡ አጥጋቢ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ እንዲኖራቸውና ፡ እሊሁም ፡ በውሳኔአቸው ፡ ላይ ፡ እንዲሰፍሩ ፡ ይገባል ። ደንቦቹን ፡ በምሉ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ በግብር ፡ ላይ ፡ ለማዋል ወይም ፡ ላለማዋል ፡ በሚወስኑ በት ፡ ጊዜ ፡ የቤተ ፡ ዘመድ ፡ ገላጋይ ፡ ዳኞቹ ፡ ሊያመዛዝኑት ፡ የሚገባቸው ፡ የፍቺ ፡ ጥያቄውን ፡ እንዲቀርብ ፡ የገፋፉትንና ፡ የከበቡትን ፡ ምክንያቶችን ፤ የበዳዩን ፡ ወገን ጥፋት ፡ ደረጃን ፡ ያላጥፊው ፡ አበርን ፡ የጠባይ ፡ አቋምንና ፡ አመራርን ፤ እንዲሁም ፡ ጥያ

ቄውን ፣ የቀሰቀሰው ፣ መነሾ ፣ ምክንያትንና ፣ የጥያቄውን ፣ የበጎና ፣ ትክክለኛ ፣ ጠባይ ፣ (ሞራል ፣ )ትይንቱን ፣ ይሆን ፣ ዘንድ ፣ ያስፈልጋል ፣ (ቍጥር ፣ ፻፲፰ ።)

ሐ/ ጋብቻ ፣ በሞት ፣ ወይም ፣ በፍቺ፣ምክንያቶች ፣ ሳይሆን ፣ በሌላ ፣ ምክንያቶች ፣ ሲፈርስ ፣ ስለማጣራት ፣ ተግባር ፤

ቍጥር ፣ ፻፲፮ ፣ ስለጋብቻ ፣ የተወሰኑት ፣ ግዴታዎች ፣ በመጣስ ፣ ጋብቻው ፣ በምጥንታ ፣ ሐግ ፣ በቀጣት ፣ ሲፈርስ ፣ ስለ ፣ አበሮቹ ፣ የሀብት ፣ ንብረት ፣ ግንኙነት ፣ ማጣራት ፣ ተግባር ፣ የሚመለከቱ ፣ ደንቦችን ፣ ይዘረዝራል ። እነዚህም ፣ ደንቦች ፣ እንደሚከተለው ፣ ናቸው ፤

ሀ/ ከቍጥር ፣ ፻፲፯ ፣ —፻፳፰ ፣ ድረስ ፣ የተመለከቱት ፣ ሐሳቦች ፣ እንደ ፣ ረዳትና ፣ መሪ ፣ ሐሳቦች፣ብቻ ፣ የሚቆጠሩ፣ናቸው ፣ እንጂ ፣ በምንም ፣ በኩል ፣ እነርሱ ፣ ከፈለሙት ፣ መንገድ ፣ እንዳይወጣ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱን ፣ የሚገቱ ፣ አይደሉም ፤

ለ/ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ የራሱን ፣ ውሳኔ ፣ የሚያደርገው ፣ በርትዕ ፣ (በፍትሕ ፣ /በትክክልነት ፣ ) መሠረት ፣ ነው ፤ እንዲሁም ፣

ሐ/ ርትዕን ፣ በሚዳኝበት ፣ (በግብር ፣ ላይ ፣ በሚያውልበት ፣ )ጊዜ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ የሚያመዛዝነው ፣ በተለይ ፣ የአበሮቹን ፣ ወይም ፣ ከነርሱ ፣ ያንዱን ፣ ታማኝነትን ፣ (ትክክለኛነት ፣ ቅንነትን ፣ ) ወይም ፣ አጭበርባሪነትን ፣ (አታላይነትን ፣) ከጋብቻው ፣ የተገኙ ፣ (እንዳለበት፣) ልጆች ፣ ጥቅምን፣እና፣አበሮቹ፣በተጋቡበት፣ ቀንና ፣ ጋብቻውን ፣ ባፈረሱበት ፣ ቀን፣መካከል ፣ ማናቸውም ፣ ሌላ ፣ ሦስተኛ ፣ ወገን ፣ (ከነርሱ ፣ ጋራ ፣ )ፍርድ ፣ ነክ ፣ የሆነን ድርጊት ፣ ፈጽሞ ፣ እንደሆነን ፣ በቅንነት ፣ (በእምነት ፣ )የተነጋገሩትን ፣ ፍርድ፣ነኩን ፣ ተግባር ፣ የፈጸሙትን ፣ ሦስተኛ ፣ ወገኖች ፣ ጥቅምን ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ በማመዘን ፣ ነገሩን፣ ይመለከታል ።

ከዚህ ፣ ላይ ፣ ሊያስታውሱት ፣ የሚገባው ፣ የጋብቻ ፣ ግዴታዎች ፣ በመጣሳቸው ፣ በምጥንታ ፣ (በቀጣት ፣ )ጋብቻው ፣ በሚፈርስበት ፣ ነገሮች ፣ ላይ ፣ ጋብቻውን ፣ የማፍረሱ ፣ ጉዳይና ፣ የሚያስከትለው ፣ የሀብት ፣ ግንኙነትን ፣ የማጣራት ፣ ተግባሩ ፣ የፍርድ ፣ ቤቱ ፣ እንጂ ፣ የቤተሰብ ፣ ገላጋይ ፣ ዳኞች ፣ ጉዳይ ፣ እንዳይደለ ፣ ነው ።

## <u>፮፤ የወዶገብነት ፣ (አጉል/ ውጥንቅጥ ፣) ኅብረት ፣ እና ፣ ሌላ ፣ ግንኙነቶች ፣ ወዶገብነት ፣ ኅብረት ፤</u>

ዘወግና ፣ ልማድ ፣ ሥርዓት ፣ ( ሕግ ፣ ) መሠረት ፣ ቀድሞ ፣ በደሞዝ ፣ በሚል ፣ ይታወቅ ፣ የነበረውን ፣ ጋብቻ ፣ ዓይነት ፣ ፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕጉ ፣ አይቀበለውም ። ይሁን ፣ እንጂ ፣ አንድ ፣ ወንድና ፣ አንዲት ፣ ሴት ፣ እንደ ፣ ባልና ፣ ሚስት ፣ ሆነው ፣ የሚገኙበትን ፣ ያንድ ፣ ላይ ፣ ኑሮ ፣ ህልውን ፣ የፍትሐ ፣ ብሔር ፣ ሕጉ ፣ በሕግ ፣ ያውቀዋል ፤ ለዚህ ፣ ህልውም ፣ የወዶ ፣–(ለምዶ ፣)–ገብነት ፣ ኅብረት ፣ (ወይም ፣ ውጥንቅጥ ፣ ፅምረት ፣ (ጥምረት፣) ወይም ፣ ኅብረት ፣ ) የሚል ፣ ስምን ፣ ሕጉ ፣ አውጥቶለታል ። እንደዚህ ፣ ያለው ፣ ጥምረት ፣ አንዳንድ ፣ ሕጋዊ ፣ ውጤቶችን ፣ ይወልዳል ፣ እንጂ ፣ የወዶ ፣ ለምዶነት ፣ ኅብረት ፣ ጋብቻ ፣ አይደለም ። ውጤቶቹም ፣ ሕጋዊው ፣ ጋብቻ ፣ ከሚወልዳቸው ፣ ውጤቶች ፣ በጣም ፣ የተለያዩ ፣ ናቸው ። የውጥንቅጥ ፣ ኅብረት ፣ ቋሚ ፣ በሕርዩው ፣ ዋጋ ፣ እንዳለው ፣ ጋብቻ ፣ ሕግ ፣ በወቀለት ፣ ሥርዓቶች ፣ መልክ ፣ የሚከናወን ፣ ( የሚሾም ፣ ) ምንም ፣ ዓይነት ፣ ጋብቻ ፣ የሌለበት ፣ መሆኑ ፣ ነው ። ውጥንቅጥ ፣ ኅብረት ፣ በቀላሉ ፣ አንዳንድ ፣ የተወሰኑን ፣ ውጤቶች ፣ የሚቀሰቅስ ፣ (የሚያነሣ ፣ ) ህልው ፣ ሁኔታ ፣ ነው ።

የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ ትርጓሜ ፡ በሚያስኬደው ፡ ክልል ፡ ውስጥ ፡ ስንመለከተው ፡ ውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ የሚኖረው ፡ አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ሲኖሩና ፡ እንደ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ በመቆጠር ፡ ሲተዳደሩ ፡ ነው ። በየዕለቱ ፡ ኑሯቸው ፡ እራሳቸውን ፡ እንደ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ አካል ፡ አድርገው ፡ በመተዳደር ፡ ሕይወታቸውን ፡ እስከ ፡ መሩ ፡ ድረስ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ተብለው ፡ መስለው ፡ በሌሎች ፡ ዘንድ ፡ ራሳቸውን ፡ ማቅረቡ ፡ (መወከሉ/ማስተዋወቁ ፡ ) አስፈላጊ ፡ አይደለም ። አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ሰርክ ፡ ቢገናኙና ፡ እንዲያውም ፡ ባልተሸፋፈነ ፡ አኳኋን ፡ (ማለት ፡ ይህ ፡ ግብራቸው ፡ በሌሎች ፡ ዘንድ ፡ ጐልቶ ፡ እስኪያውተመትሙበትና ፡ እስኪታወቅ ፡ ድረስ ፡ ) እንዲሁም ፡ የተደጋገመ ፡ ሩካቤ ፡ ሥጋ ፡ ዝምድናዎች ፡ (የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነቶች ፡ ) ቢኖራቸው ፡ እንኳ ፡ ቅሉ ፡ ይህ ፡ ሀልው ፡ በራሱ ፡ ሱታፌውን ፡ እንደ ፡ ወዶ ፡ ለምዶ ፡ ኅብረት ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ ለማስቆጠር ፡ በቂ ፡ አይደለም ፤ ውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ የሚያስከትለውን ፡ የሕግ ፡ ውጤቶችንም ፡ ሊወልድ ፡ አይችልም ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፰ ።)

ውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ መኖሩን ፡ ማረጋገጡ ፡ የምስክር ፡ ማስረጃ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፤ ይኸም ፡ የምስክር ፡ ማስረጃ ፡ የሚነጻጸረው ፡ ከሌሎች ፡ ከካባቢያቸው ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ በላቸው ፡ የማኅበራዊ ፡ አኗኗር ፡ ደረጃ ፡ መጠን ፡ ነው ። ይህም ፡ ያኗኗር ፡ አቋም ፡ የወንድየውና ፡ የሴትዮዋ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ቤተ ፡ ዘመዶች ፡ እና ፡ ጎረቤቶች ፡ በእውነቱ ፡ ሳይጋቡ ፡ እንደተጋቡ ፡ እንደሚኖሩ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አድርገው ፡ ሲገምቷቸው ፡ (ሲቆጥሯቸው ፡ ) ማለት ፡ ነው ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፲፰ ።) እንግዲህ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ያኗኗር ፡ አቋም ፡ እንዳለ ፡ የሚያስረዳው ፡ የታመኑ ፡ ምስክሮችን ፡ በማስመስከር ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ምስክሮችን ፡ አቅርቦ ፡ ያኗኗር ፡ አቋም ፡ አለመኖሩን ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ምስክር ፡ ማስረጃ ፡ ሲታጣ ፡ ከጽሑፍ ፡ ነጋሪ ፡ ባለሥልጣን ፡ ፊት ፡ (በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ «በግልጽ ፡ የታወቀ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ ሰው ፡ » ያለውን ፡ ነው ፤) በተፈጸመ ፡ የጽሑፍ ፡ ክንውን ፡ ያኗኗር ፡ አቋምን ፡ ያስረዷል ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፲፱ ፡ እና ፡ ፯፻፳ ።)

<u>የወዶ ፡ ገብነት ፡ ኅብረት —</u>

ሀ/ በወንድየውና ፡ በሴትዮዋ ፡ መካከል ፡ ኑሮን ፡ ለመጠበቅ ፡ የመተዳደሪያ ፡ አበል ፡ ግዴታን ፤

ለ/ በወንድየውና ፡ በሴትዮዋ ፡ መካከል ፡ የጋራ ፡ ሀብት  ንብረትን ፤

ሐ/ በወንድየውና ፡ በሴትዮዋ ፡ መካከል ፡ ማናቸውንም ፡ የውርስ ፡ መብቶችን ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፲፬ ፡ ፯፻፲፪ ፡ እና ፡ ፯፻፲፫) ፡ አይፈጥርም ።

ውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ በደንበኛው ፡ ጋብቻ ፡ እንደተመለከተው ፡ ያለ ፡ የጋብቻ ፡ ዝምድናን ፡ የመሰለ ፡ መተሳሰሪያን ፡ አያስከትልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ለሕዝብ ፡ በጎ ፡ ኑሮ ፡ የሕዝብ ፡ ሰላም ፡ ሥርዓትን ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲባል ፡ በውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ የሚኖሩት ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ እንደተጋቡ ፡ ሰዎች ፡ ታይተው ፡ የወንዱና ፡ የሴቲቱ ፡ ዘመዶች ፡ (የጋብቻ ፡ ዝምድናን ፡ ወሰን ፡ ጥሰው ፡ ) እንዳይጋቡ ፡ ክልክል ፡ ናቸው ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፲) ። ባንድ ፡ በኩል ፡ የውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ ዋጋ ፡ ከደንበኛው ፡ ጋብቻ ፡ ጋራ ፡ (እኩል ፡ ) ተመጣጣኝ ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ከኅብረቱ ፡ ለሚወለዱት ፡ ልጆች ፡ አባትነትና ፡ እናትነት ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ለተወለዱት ፡ ልጆች ፡ የሚሆኑት ፡ ደንቦች ፡ ከውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ ለተወለዱት ፡ ልጆችም ፡ ይሆናሉ ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፲፭) ።

የውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ ያለ ፡ አንዳች ፡ ያፈጸጸም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በማንም ፡ ጊዜ ፡ ሊፈርስ ፡ ይችላል ። የቤተ ፡ ሰቡ ፡ ገላጋይ ፡ ዳኞቹም ፡ ከውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ የሚነሱትን ፡ ነገሮች ፡ ለማየት ፡ ምንም ፡ ሥልጣን ፡ የላቸውም ፤ ከውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ የሚነሱትን ፡ ክርክሮች ፡ ሁሉ ፡ ለማየት ፡ ችሎታ ፡ ያላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፴) ። ኅብረቱን ፡ የምትሰርዘው ፡ (የምትሽረው ፡ ) ሴቲቱ ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ ለወንድ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ካሣ ፡ ወይም ፡ ኪሣራ ፡ እንድትከፍል ፡ አይደረግም ፤ ወይም ፡ በኅብረቱ ፡ ወራት ፡ ወንዱ ፡ አበርክቷት ፡ ሊሆን ፡ የሚችለውንም ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ መልሳ ፡ እንድታስረክበው ፡ አይደረግም ። ኅብረቱን ፡ የሚያፈርሰው ፡ ወንድየው ፡ ሲሆን ፡ ግን ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፲፯ ፡ መሠረት ፡ ሴቲቱ ፡ ለሦስት ፡ ወር ፡ ጊዜ ፡ ኑሮ ፡ መተዳደሪያ ፡ ወጭዎቿ ፡ በቂ ፡ የሚሆናትን ፡ ገንዘብ ፡ ወንዱ ፡ እንዲከፍላት ፡ ለመጠየቅ ፡ መብት ፡ አላት ፡ (እስከዚህ ፡ ከፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ በአማርኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። በእንግሊዝኛው ፡ ትርጕም ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡ ስድስት ፡ ወራት ፡ ተብሏል ። በሕጉም ፡ ፈረንሣይ ፡ ጽሑፍ ፡ ዋና ፡ ቅጅ ፡ ስድስት ፡ ወራት ፡ ተብሏል ።)

## ከማእሰረ ፡ ጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ግንኙቶች ።

በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ መሠረት ፡ የሕግ ፡ አቋም ፡ የተሰጣቸው ፡ የወንድና ፡ የሴት ፡ ግንኙነቶች ፡ (ሀ) ፡ ጋብቻ ፡ እና ፡ (ለ) ፡ ውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ ብቻ ፡ ነው ። በጋብቻ ፡ ረገድ ፡ ሦስት ፡ የጋብቻዎች ፡ አይነቶች ፡ አሉ ፡ ከእነዚህም ፡ የተለያዩ ፡ ሌሎች ፡ ከቶ ፡ የሉም ፤ እነዚህም ፡ ብሔራዊ ፡ የሃይማኖትና ፡ የልማድ ፡ ጋብቻ ፡ የተባሉት ፡ ናቸው ። በቍጥር ፡ ፫ሺ፫፻፹፪ ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ (ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡) ከመጽናቱ ፡ በፊት ፡ ይሠራበቸው ፡ የነበሩት ፡ የልማድ ፡ ሕጐች ፡ ሁሉ ፡ (ከነዚያ ፡ ውስጥ ፡ በዚህም ፡ ሕግ ፡ ጸድቀው ፡ ከቀሩት ፡ ልማዶች ፡ በቀር ፡ ) መሻራቸውን ፡ ማስታወስ ፡ ያስፈልጋል ። ቍጥር ፡ ፯፻፳፩ ፡ በወንድና ፡ በሴት ፡ መካከል ፡ ያለን ፡ የግንኙነትን ፡ ይዘት ፡ አጥብቆ ፡ ሲያጠይቅ ፤ ግንኙነቱ ፡ የተነሣው ፡ ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከወዶ–ለምዶ ፡ (ከውጥንቅጥ ፡ ) ኅብረት ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ በወንድና ፡ በሴት ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ግንኙነት ፡ ምንም ፡ አንዳች ፡ ውጤት ፡ እንደሌለው ፡ ያረጋግጣል ። ከሕጋዊ ፡ ወይም ፡ ከውጥንቅጥ ፡ ጥምረት ፡ ውጭ ፡ የሆኑ ፡ ግንኙነቶች ፡ ምንም ፡ አንዳች ፡ የሕግ ፡ ውጤት ፡ ስለሌላቸው ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ በምንም ፡ ዓይነት ፡ ክርክር ፡ ላይ ፡ ( በሌላ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ ) በወንድና ፡ በሴት ፡ መካከል ፡ ግንኙነት ፡ አለ ፡ የሚል ፡ ይዘትን ፡ ሊያነሣበት ፡ አይችልም ። እነሆ ፡ ቆየት ፡ ብለን ፡ እንደምንረዳው ፡ ከአንዲት ፡ ( በሕጋዊ ፡ መንገድ ፡ ) አንድ ፡ ወንድ ፡ ጋራ ፡ ከተጋባች ፡ ሴት ፡ የተወለደ ፡ ሕፃን ፡ አባቱ ፡ የዚያችው ፡ ሴት ፡ ባል ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ያንንም ፡ ልጅ ፡ ሊክድ ፡ የሚችለው ፡ አባት ፡ ያው ፡ ብቻ ፡ ነው ። በቍጥር ፡ ፯፻፳፩ ፡ (፱) ፡ መሠረት ፤ ልጁ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ለመካድ ፡ ለሚሻ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የሕፃኑ ፡ እናት ፡ በእውነቱ ፡ ከሌላ ፡ ወንድ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነቶችን ፡ ፈጽማለች ፡ ብሎ ፡ ለማለት ፡ አይቻለውም ። ምክንያቱም ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ የተነሣ ፡ ሊሆን ፡ አይችልምና ፡ ነው ።

ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ ውጭ ፡ በሚገኝ ፡ ግንኙነት ፡ ባሉ ፡ አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ የተወለዱ ፡ ልጆችን ፡ ስለሚመለከቱት ፡ ጉዳዮች ፤ ቍጥር ፡ ፯፻፳፩ ፡ (፫) ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉት ፡ ልጆች ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የመተሳሰር ፡ ዝምድናዎች ፡ ያሏቸው ፡ ከናታቸው ፡ ጋራ ፡ ብቻ ፡ መሆኑን ፡ ያመለክታል ። ይህ ፡ መሪ ፡ ሐሳብ ፡ ከቍጥር ፡ ፯፻፺፰ – ፯፻፵፯ ፡ እንደ ፡ ተደነገጉት ፡ የባሕርይ ፡ አባቱ ፡ ልጅነቱን ፡ ላወቀለት ፡ ልጅ ፡ አይሆንም ፡ ወይም ፡ ልጅን ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በጉድፈቻ ፡ ልጅነት ፡ ሲቀ

በለው ፡ በፍርድ ፡ ረገድ ፡ ልጅ ፡ በዝምድና ፡ (ግንኙነት ፡ ) የተሳሰረው ፡ ከናቲቱ ፡ ጋራ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከተቀበለውም ፡ አባት ፡ ወይም ፡ በጉድፈቻ ፡ ልጅነት ፡ ከተቀበለው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ስለሚሆን ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ መሪ ፡ ሐሳብ ፡ ለእንደዚህ ፡ ላለው ፡ ልጅ ፡ አያገለግልም ።

## ፯ ፡ በጋብቻዎች ፡ በፍቺዎችና ፡ በወዶለምዶ ፡ ኅብረቶች ፡ ስለሚነሡት ፡ ክርክሮች ።

በቍጥር ፡ ፯፻፳፪ ፡ እና ፡ ከተከታታዮቹ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕጉ ፡ በትጭጭቶች ፡ በጋብቻዎችና ፡ በውጥንቅጥ ፡ ጽምረት ፡ የሚነሡት ፡ ክርክሮች ፡ (ጭቅጭቆች ፡) ከንውን ፡ መልክ ፡ የሚዳኙትን ፡ ደንቦች ፡ መሥርቷል ። በሕግ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ መተጫጨት ፡ ተደርጎ ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ የጋብቻው ፡ በዓል ፡ ተሹሞ ፡ እንደሆነና ፡ እንደ ዚህ ፡ ከሆነ ፡ ዘንዳም ፡ ጋብቻው ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ እንደሆነ ፤ እንዲሁም ፡ ወይም ፡ በሁለት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ ተዘርግቶ ፡ እንደሆነ ፡ ለመወሰን ፡ የዳኝነት ፡ ምሉ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ፍርድ ፡ ቤቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፳፪ ፡ ፯፻፳፬ ፡ ፯፻፴) ። ደግሞም ፡ ፍርድ ፡ ቤቶቹ ፡ ከውጥንቅጥ ፡ ጽምረት ፡ የሚነሡትን ፡ ጉዳዮች ፡ ሁሉ ፡ ለመወሰን ፡ ፍጹም ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከትጭጭት ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ በሚነሡት ፡ ክርክሮች ፡ ረገድ ፡ ክርክሮቹ ፡ በመዠመሪያው ፡ ክፍል ፡ የሚታዩት ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ ዳኞች ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ያስፈልጋል ።

በመተጫጨት ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ የትጭጭት ፡ ስምምነትን ፡ በማፍረስ ፡ ምክንያት ፡ ስለሚነሡት ፡ ክርክሮች ፡ ገላጋይ ፡ ዳኞቹ ፡ በትጭጭቱ ፡ ጊዜ ፡ ምስክሮች ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። በመዠመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ምስክርነት ፡ ተደልድለው ፡ የነበሩ ፡ ካሉ ፡ ገላጋይ ፡ ዳኞቹ እንደነዚህ ፡ ያሉት ፡ ምስክሮች ፡ ይሆናሉ ። በትጭጭቱ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ቆየት ፡ ብለው ፡ (ባለጉዳይ) ወገኖቹ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ እንዲሆኑላቸው ፡ ከመደልደል ፡ የሚያግዳቸው ፡ አንዳችም ፡ ምክንያት ፡ የለም ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፳፫) ።

በጋብቻው ፡ ገራት ፡ ውስጥ ፡ በሚነሡት ፡ ነገሮች ፡ የቤተሰቡ ፡ ገላጋይ ፡ ዳኞቹ ፡ በጋብቻው ፡ ጊዜ ፡ ምስክሮች ፡ ሁነው ፡ የነበሩት ፡ ናቸው ። እንደዚሁም ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ የመዠመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ምስክሮች ፡ በመሆን ፡ ተደልድለው ፡ የነበሩ ፡ ካሉ ፡ የቤተ ዘመዱ ፡ ገላጋይ ፡ ዳኞቹ ፡ እነዚሁ ፡ የመዠመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ምስክሮች ፡ መሆን ፡ አለባቸው ። በሚጋቡበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ዘግየት ፡ ብለው ፡ ለምሳሌ ፡ ክርክሩ ፡ በግልጽ ፡ በሚነሣበት ፡ ጊዜ ፡ አበሮቹ ፡ ክርክሩን ፡ እንዲያዩላቸው ፡ ገላጋይ ፡ ዳኞች ፡ የሚሆኑ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎችን ፡ ሊደለድሉ ፡ ይችላሉ ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፳፭) ። ደግሞም ፡ በሞት ፡ መለየት ፡ ጋብቻው ፡ ሲፈርስ ፡ አስቀድመው ፡ (በመዠመሪያው ፡ ክፍል) ክርክሮቹን ፡ ለማየት ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ ናቸው ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፳፮) ። ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ክርክር ፡ በጋብቻው ፡ ወራት ፡ ሳይሆን ፡ ፍቺው ፡ ከተለፈፈ ፡ በኋላ ፡ ቢነሣ ፡ ክርክሩ ፡ ከነዚያው ፡ ፍቺውን ፡ ከበየኑት ፡ ገላጋይ ፡ ዳኞች ፡ ፊት ፡ ይቀርባል ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፳፯) ። የቤተሰቡ ፡ የሽምግልና ፡ ዳኞቹ ፡ ሕግ ፡ በሚፈቅድላቸው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከውሳኔ ፡ ለመድረስ ፡ አቅቷቸው ፡ ፍቺውን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ በሚበይንበት ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሕጉ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የተለየና ፡ የጐላ ፡ ድንጋጌ ፡ አላደረገም ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፴፯ን ፡ ይመለከቷል)። ነገር ፡ ግን ፡ በእንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ነገሮች ፡ ከፍቺው ፡ በኋላ ፡ የሚነሣው ፡ ክርክር ፡ ለፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲቀርብ ፡ ይገባል ። ከውጥንቅጥ ፡ ኅብረት ፡ የሚነሡት ፡ ክርክሮች ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚቀርቡ ፡ ናቸው ። (ቍጥር ፡ ፯፻፴) ።

የሽምግልና ፡ (ገላጋይ) ዳኞች ፡ ቍጥር ፡ እንደደንቡ ፡ ለያንዳንዱ ፡ አበር ፡ ሁለት ፡ መሆን ፡ ይገባቸዋል ። አንድ ፡ ገላጋይ ፡ በሞት ፡ የተለየ ፡ ወይም ፡ ክርክሩን ፡ ሳያዘገይ ፡ ለመወሰን ፡ በቂ ፡ ሁኖ ፡ ባልተገኘ ፡ ጊዜ ፡ በዚያው ፡ በተመደበበት ፡ መልክና ፡ ቅጥ ፡ (ሥርዓት) ዓይነት ፡ ሌላ ፡ እንዲተካበት ፡ ያስፈልጋል ፤ ይኸም ፡ አንድ ፡ ገላጋይ ፡ ከአበሮቹ ፡ ባንዱ ፡ ተደልድሎ ፡ ወይም ፡ (በጋብቻው ፡ በዓል) ከአበሮቹ ፡ ውስጥ ፡ ላንዱ ፡ ምስክር ፡ ኑሮ ፡ እንደሆነ ፡ ያው ፡ አበር ፡ እርሱን ፡ የሚተካለት ፡ ሌላም ፡ ሰው ፡ ሊጠራ ፡ (ሊደለድል)ይችላል ፡ ማለት ፡ ነው ። የሚያስፈልገው ፡ የገላጋይ ፡ ዳኞች ፡ ቍጥር ፡ ቢኖር ፡ ግን ፡ አንዱ ፡ እንደገላጋይ ፡ ዳኛ ፡ ሁኖ ፡ መቀመጡን ፡ ባይፈልግ ፡ ወይም ፡ እንዳይሆን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ቢያስገድደው ፤ እርሱን ፡ የሚተካ ፡ ሌላን ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሊመድብ ፡ ይችላል ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፴፫) ። ክርክሩን ፡ በመወሰን ፡ ያሉባቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ ለማከናወን ፡ ያስችላቸው ፡ ዘንድ ፤ ገላጋዮቹ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተነጋግረው ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፤ አንድ ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ተጨማሪ ፡ ገላጋዮችን ፡ ለመደልደል ፡ ይችላሉ ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፴፬) ። በማናቸውም ፡ ክርክር ፡ የተነሣ ፡ እንዲወስኑ ፡ አበሮቹ ፡ ገላጋዮችን ፡ ለመሰየም ፡ ቢስማሙና ፡ በአደላደሉ ፡ መግባባት ፡ ቢሳናቸው ፡ ድልድሉ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ እንዲወሰን ፡ ይገባል ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፴፭) ። አንድ ፡ ገላጋይ ፡ እንዲያቀርብ ፡ የተፈለገ ፡ አበር ፡ ሽማግሌውን ፡ እንዲያቀርብ ፡ ሌላው ፡ አበር ፡ ከጠየቀበት ፡ ቀን ፡ አንስቶ ፡ በአሥራ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ማቅረብ ፡ ቢያቅተው ፤ ባለጉዳዩ ፡ አበር ፡ ባቀረበው ፡ አቤቱታ ፡ መሠረት ፡ ገላጋዩን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ይደለድላል ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፴፮) ። በሕግ ፡ ተለይቶ ፡ በተቆረጠው ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ለአእምሮ ፡ ሚዛን ፡ አጥጋቢ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ገላጋዮቹ ፡ ውሳኔ ፡ ለመስጠት ፡ ቢሳናቸው ፤ ከአበሮቹ ፡ ባንዱ ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ክርክሩ ፡ ከዳኝነቱ ፡ ሥልጣን ፡ ፊት ፡ የፈሰሰለት ፡ (የቀረበለት) መሆኑን ፡ አውቆ ፡ ለመወሰን ፡ ይችላል ፡ (ቍጥር ፡ ፯፻፴፯) ። ጉዳዩ ፡ በፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የሚታወቀው ፡ ከጋብቻው ፡ በሚነሣው ፡ ክርክር ፡ ገላጋዮቹ ፡ ከውሳኔ ፡ መድረስ ፡ ሲያቅታቸው ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዳኝነት ፡ ሥልጣን ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ የሥልጣን ፡ ተቀጽላ ፡ ሁኖ ፡ የቀረ ፡ ይመስላል ። የቤተሰቡ ፡ ገላጋዮች ፡ ውሳኔ ፡ በይግባኝ ፡ ለፍርድ፡ቤት ፡ ሊመራ ፡ የሚችል ፡ ነው ፤ ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ሊገለብጠው ፡ (ሊሽረው) የሚችለው ፡ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ ውሳኔ ፡ በጉቦና ፡ በተንኮል ፡ ወይም ፡ በማጭበርበር ፡ የተበከለ ፤ ወይም ፡ ውሳኔው ፡ በግልጽ ፡ ከአእምሮ ፡ ሚዛን ፡ የራቀ ፡ (ለምሳሌ ፡ የቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ገላጋዮች ፡ ከቍጥር ፡ ፯፻፺፯—፯፻፺፰ ፡ የተመለከቱትን ፡ ደንቦች ፡ ባልተከተሉ ፡ ጊዜ)፡ ሲሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ።